# ኢትዮጵያ

# የሽግግር ፍትህ የፖሊሲ አቅጣጫ አማራጮች

ከባለድርሻ አካላት ግብአት ለመሰብሰብ የተዘጋጀ

የሽግግር ፍትህ የባለሙያዎች የስራ ቡድን

ጥር 2015 ዓ.ም.
አዲስ አበባ

የሽግግር ፍትህ
TRANSITIONAL JUSTICE

## ማውጫ


መግቢያ
ክፍል አንድ፡ በኢትዮጵያ የሽግግር ፍትህ ታሪካዊ ዳራ እና አስፈላጊነት
1.1. የሽግግር ፍትህ ሂደት ዓለም-አቀፋዊ ተመክሮ 3
1.2. የሽግግር ፍትህ ሂደት ተመክሮ በኢትዮጵያ 4
1.3. በኢትዮጵያ የሽግግር ፍትህ አስፈላጊነት 8
ክፍል ሁለት፡ የሽግግር ፍትህ ስልቶች እና የፖሊሲ አቅጣጫ አማራጮች
2.1. መግቢያ 9
2.2. ክስ 10
2.2.1. ጠቅላላ 10
2.2.2. የትኛዎቹ ጉዳዮች ያስከስሳሉ? 10
2.2.3. በየትኛዎቹ አጥፊዎች ላይ ክስ ይመሰረታል? 12
2.3. ተቋማዊ ጉዳዮች፡- የወንጀል ምርመራ፣ ክስ የመመስረት እና የፍርድ ሂደትን ማን ያከናውነዋል?
2.3.1. ጠቅላላ 13
2.3.2. ፍርድ ቤቶች 14
2.3.3. ምርመራ እና ክስ 15
2.3.4. የህግ ማሻሻያ ተግባራት፡ በሰብአዊነት ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎችን በሀገራችን ህግ ማካተት 16
2.4. እውነትን ማፈላለግ እና ይፋ ማውጣት 17
2.4.1. ጠቅላላ 17
2.4.2. እውነትን በማጣራት ሂደት ዋና ዋና ተግባራት ምንድን ናቸው? 17
2.4.3. ተቋማዊ ጉዳዮች፡ እውነትን የማጣራት ሂደትን ማን ያከናውነዋል? 17
2.5. እርቅ 19
2.5.1. ጠቅላላ 19
2.5.2. በሽግግር ፍትህ ሂደት ሊከናወኑ የሚችሉ የእርቅ አይነቶች 19
2.5.3. ተቋማዊ ጉዳዮች፡ የእርቅ ሂደትን ማን ያከናውነው? 20
2.6. ምህረት 21
2.6.1. ጠቅላላ 21
2.6.2. የምህረት ሂደት ቅድመ-ሁኔታዎች ምን ሊሆኑ ይችላሉ? 21
2.6.3. ተቋማዊ ጉዳዮች፡ ምህረት የመስጠት ሂደትን ማን ያከናውነዋል? 22
2.6.4. ምህረት በህግ አግባብ የሚሰጥበት ሁኔታ 23
2.7. ማካካሻ 24
2.7.1. ጠቅላላ 24
2.7.2. በማካካሻ ስርአት ምን አይነት የማካካሻ አይነቶች ሊተገበሩ ይችላሉ? 24
2.7.3. የማካካሻ ስርአት ለመገንባት የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት 25
2.7.4. ተቋማዊ ጉዳዮች፡- የማካካሻ ስርአትን ማን ይመራዋል/ያስተባብረዋል? 26
2.8. ተቋማዊ ማሻሻያ 27
2.8.1. ጠቅላላ 27
2.8.2. በሽግግር ፍትህ ሂደት የተቋማዊ ማሻሻያ ተግባራት ምን ምን ሊያካትቱ ይችላሉ? 28
2.8.3. ተቋማዊ ጉዳዮች፡ የተቋማዊ ማሻሻያ ተግባራት በማን ይከናወናሉ? 28
2.9. ውሳኔ የሚያስፈልጋቸው ጉዳዮች 29
2.9.1. የሽግግር ፍትህ ሂደት ከየትኛው ጊዜ ይጀምር? 29
2.9.2. በሽግግር ፍትህ ሂደት የክልሎች/ከተማ መስተዳደሮች ሚና 33


Draft

2.9.3. የባህላዊ ፍትህ ሥርአቶች ሚና 33
ክፍል ሶስት፡ የሽግግር ፍትህ ሂደት ሊመራባቸው የሚገቡ መርሆዎች እና የማስተባበር አደረጃጀት አማራጮች
3.1. የሽግግር ፍትህ ሂደት ሊመራባቸው የሚገቡ መርሆዎች 34
3.2. የማስተባበር አደረጃጀት አማራጮች 35
4. ማጠቃለያ 36

Draft

## መግቢያ

ከእርስ በእርስ ጦርነት፣ ግጭት እና ጭቆና በመውጣት - በፖለቲካና በዲሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ትርጉም ያለው ሽግግር ለማድረግ በሞከሩ ሀገራት የሽግግር ፍትህ ሂደቶች ተግባራዊ ተደርገዋል። የሽግግር ፍትህ ስርአት መዘርጋቱ ዘላቂ ሰላም፣ እርቅ እና ፍትህ በማስገኘት ረገድ ከፍተኛ አስተዋፅዎ አበርክቷል። የተባበሩት መንግስታት ድርጅት - ሀገራትና ማህበረሰቦች ከደረሰባቸው መጠነ-ሰፊ የመብቶች ጥሰት ሁኔታ በመውጣት - ተጠያቂነትን፣ ፍትህን እና እርቅን ባማከለ መልኩ የሚያከናውኑት የሽግግር ፍትህ ሂደትን መደገፍ እንደሚገባው በመግለጽ[1] - በተለያዩ ሀገራት የተሞከሩ የሽግግር ፍትህ ሂደቶችን አግዟል። በአፍሪካም በ2011 ዓ.ም በአዲስ አበባ የፀደቀው የአፍሪካ ኅብረት የሽግግር ፍትህ ፖሊሲ ማዕቀፍ - የሽግግር ፍትህ - ሀገራት የተለያዩ (መደበኛ እና ባህላዊ/መደበኛ ያልሆኑ) የፖሊሲ እርምጃዎችን እና ተቋማዊ አሠራሮችን በመጠቀም - ያለፉ ጥሰቶችን፣ ክፍፍሎችንና አለመመጣጠኖችን ለማስወገድና ለደኅንነትም ሆነ ለዴሞክራሲያዊና ማህበራዊ-ኢኮኖሚያዊ ለውጥ ሥርዓት ግንባታ ምቹ ሁኔታዎችን ለመፍጠር የሚደረግ ጠቃሚ እና አስፈላጊ ሂደት እንደሆነ ይገልጻል።[2]

ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት ወዲህ - በተለያዩ የአለም ሀገራት የተለያየ ይዘት ያላቸው የሽግግር ፍትህ ስራዎች ተግባራዊ ሆነዋል። በተለይም በደቡብ አሜሪካና በአፍሪካ ሀገራት የሽግግር ፍትህ አሰራሮች በተለያየ መጠን ተተግብረው በርካታ ተመክሮዎች ተቀምረዋል። ከነዚህ አገሮች የተሳካ የሽግግር ፍትህ ልምድም ሌሎች ሀገራት ሊያከናውኗቸው የሚገቡ ተግባራት እና ሊከተሏቸው የሚገቡ ሂደቶችን ለመለየት ተችሏል።

በሀገራችን ኢትዮጵያም በተለያዩ ጊዜያት የሽግግር ፍትህ ሂደት አላባዎችን ተግባራዊ ለማድረግ ሙከራ ተደርጓል። የሽግግር ፍትህ ስልቶችን አላማ፣ ግብ እና የሚኖራቸውን መስተጋብር የሚቃኝ የሽግግር ፍትህ ፖሊሲ ስላልነበር - አማራጮቹ በተንጠባጠበ እና በማይመጋገብ መልኩ እንዲተገበሩ ሆኗል። ይህም የሚፈለገውን ያህል ውጤታማ እንዳይሆኑ አስተዋፅኦ አደርጓል። ከዚህ አንፃር - በሀገራችን ከተተገበሩ ሙከራዎች በመማር፣ የተገኘውን ውጤት እና ልምድ በመቀመር፣ ዓለምአቀፍ ተመክሮዎችን እና ምክረ ሀሳቦችን ባካተተ መልኩ - የሀገራችንን ፖለቲካዊ እና ማህበራዊ ሁኔታ መሰረት በማድረግ - በሀገራችን የሽግግር ፍትህ በምን አግባብ ሊመራ እና ሊተገበር ይገባል የሚለውን ጥያቄ የሚመልስ የሽግግር ፍትህ ፖሊሲ ማዘጋጀት አስፈላጊ ሆኗል።

ለዚህም መነሻ የሚሆን ፅሁፍ በዘርፉ መጠነ-ሰፊ ጥናት ባደረጉ ምሁራን እና ባለሙያዎች ተዘጋጅቶ ቀርቧል። የጥናት ፅሁፉን መሰረት በማድረግም - በቀጣይ ለሚዘጋጀው ፖሊሲ አማራጭ ሊሆኑ የሚችሉ ሀሳቦችን ለውይይት ለማቅረብ እና ግብዓት ለመሰብሰብ ይቻል ዘንድ ይህ የመነሻ ሰነድ ተዘጋጅቷል። ይህ ሰነድ ሶስት ክፍሎች ያሉት ሲሆን - በክፍል አንድ የሽግግር ፍትህን ታሪካዊ ዳራ እና ሀገራችን ላለችበት ውቅታዊ ሁኔታ ያለውን አስፈላጊነት፣ በክፍል ሁለት በሀገራችን የሽግግር ፍትህን በተመለከተ ያሉትን አማራጮች እና ምክረ ሀሳቦችን፣ እንዲሁም በክፍል ሶስት የሽግግር ፍትህ ሂደቱ ሊመራባቸው የሚገቡ መርሆዎች እና የማስተባበር አደረጃጀት አማራጮች ቀርበዋል።

## ክፍል አንድ

## በኢትዮጵያ የሽግግር ፍትህ ታሪካዊ ዳራ እና አስፈላጊነት

### 1.1. የሽግግር ፍትህ ሂደት ዓለም-አቀፋዊ ተመክሮ

በሽግግር ውስጥ ያለ ማህበረሰብ ከነበረበት ሁኔታ ሲወጣ ወይም ለመውጣት በሚደረግ ሂደት ውስጥ የሚያጋጥመው ፈተና በግጭት፣ በጦርነት ወይም ጨቋኝ ሥርዓት በነበረበት ወቅት ለተፈፀመ ጥቃት፣ መጠነ-ሰፊ የሰብአዊ መብቶች

[1] United Nations Approach to Transitional Justice, Guidance Note of the Secretary- General, 2010.

[2] The AU Transitional Justice Policy 2019.

*ጥሰት እና በደል የተሟላ መፍትሄ መስጠት መቻል ነው። ይህም በዋናነት ሙሉ ፍትህ የሚሰጥበትን መንገድ መዘርጋት እና ማህበረሰቡ ተመልሶ ወደቀደመ ሁኔታው እንዳይመለስ ለማድረግ የሚያስችል ዘላቂ ሰላም፣ እርቅ፣ መረጋጋት እና የህግ የበላይነት የሰፈነበት ሥርዓት መገንባት የሚቻልበትን ሁኔታ የሚመለከት ነው።*

*በዚህ አውድ ውስጥ በነበሩ ሀገራት የተለያዩ ስልቶች ተግባራዊ ተደርገዋል። በተለይም ክስ እና ቅጣት ላይ ትኩረት በማድረግ ጊዜያዊ ፍርድ ቤቶችን በማቋቋም አጥፊዎችን በመቅጣት ላይ ያተኮሩ ሂደቶች የተተገበሩ ሲሆን፣ ጊዜያዊ ዓለም-አቀፍ ፍርድ ቤቶች በመመስረት፣ አጥፊዎችን በዓለም አቀፍ የወንጀለኞች ፍርድ ቤት በማቅረብ፣ ወይም በሀገር ውስጥ ልዩ ፍርድ ቤቶችን በማቋቋም ጭምር በሀገር ደረጃ ፍርድ የመስጠት ተመክሮዎች በስፋት ታይተዋል።*

*ይሁንና በተለይ በሽግግር ላይ ባሉ መጠነ-ሰፊ እና ውስብስብ በደሎች በነበሩባቸው አገራዊ አውዶች አጥፊዎችን መቅጣት ላይ ብቻ ያተኮሩ የፍትህ ሂደቶች መሰረታዊ ጉድለቶች እንደነበሩባቸው ማየት ተችሏል። በዚህ ረገድ ሁለት ዋና ዋና ክፍተቶችን ማንሳት ይቻላል።*

*አንደኛ፡- እነዚህ ሂደቶች በወንጀል ክስ አማካኝነት የአጥፊዎችን ተጠያቂነት በማረጋገጥ ላይ በማተኮራቸው ሀገርን ለመፈወስ አለመቻላቸው፣ ስለጥሰቶቹ መሰረታዊ ምክንያቶች አይነት እና ስፋት በተገቢዉ ሁኔታ አለመሰነዳቸው፤ እንዲሁም ተጎጂዎች እና ማህበረሰቡን ለማከም በቂ ትኩረት አለመስጠታቸው ነው። ይህም አካሄድ የፍትህ ሂደቶቹ ዘላቂ ሰላም እና እርቅ በመፍጠር ረገድ ተገቢ አስተዋፅኦ እንዳይኖራቸው አድርጓል።*

*ሁለተኛ፡- መጠነ-ሰፊ የሰብአዊ መብቶች ጥሰት፣ ለአመታት የዘለቀ መንግስታዊ ጭቆና እና የእርስ በርስ ግጭት በነበሩባቸው አውዶች ሁሉንም አጥፊዎች ለፍርድ ማቅረብ የማይቻል በመሆኑ የተወሰኑትን ብቻ የሚቀጣ የፍትህ ሂደት በተጎጂዎች ዘንድ በቂ እና የተሟላ ተደርጎ ስለማይቆጠር - ምሉእ ፍትህ ለመስጠት የሚያስችል ሂደት እንዳይሆን ምክንያት ሆኗል።*

*ስለሆነም እነዚህን በወንጀል ክስ ላይ ብቻ የተመሰረቱ የፍትህ ሂደት ክፍተቶችን በመሙላት - ለዘላቂ ሰላም አስተዋፅዎ የሚያደርግ እና አጥፊዎችን ከመቅጣት ባሻገር ሁለንተናዊ ጠቀሜታን የሚሰጥ የሽግግር ፍትህ ማዕቀፍ አዳዲስ ዘዴዎችን እና መንገዶች ይዞ ብቅ ብሏል። ከቅርብ ጊዜ ወዲህም ለጉልህ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች ክስን እንደ አንድ የሽግግር ፍትህ ስልት ተጠቅሞ ፍትህን/ተጠያቂነትን ከማስፈን በተጨማሪ - የሽግግር ፍትህ ሂደቱ እውነት የሚጣራበት እና ይፋ የሚወጣበት፣ እርቅ የሚሰፍንበት፣ የማካካሻ እርምጃ እና የተቋማት ለውጥ የሚካሄድበት ስልት ሆኖ በስፋት ስራ ላይ እየዋለ ነው። እነዚህ ማእቀፎች እርስ በርስ የሚተካኩ ሳይሆኑ - አንዱ ሌላውን የሚደግፍ እና የሚመጋገቡ በመሆናቸው - በሽግግር ላይ ያሉ ሀገራት እንደ አውዳቸው እና ችግሮቻቸው አይነት ሁሉን-አቀፍ እና መጠነ-ሰፊ የሽግግር ፍትህ አላባዎችን እንዲጠቀሙ ይመከራል።*

*የሽግግር ፍትህ በተለያዩ የዓለም ሀገራት በተለያዩ ጊዜያት ተግባራዊ የተደረገ በመሆኑ በርካታ መልካም ተመክሮዎችን ለመቀመር እና ለመማር እድል የሰጠ በመሆኑ አሁን አሁን የሚተገበሩ የሽግግር ፍትህ ሂደት አላባዎች፣ አካሄዶች እና መንገዶች በልምድ ላይ የተመሰረቱ እና የጎለበቱ እንዲሆኑ አስችሏል።*

## 1.2. *የሽግግር ፍትህ ሂደት ተመክሮ በኢትዮጵያ*

*ሀገራችን ኢትዮጵያ በተለያዩ ጊዜያት በሽግግር ሁኔታ ውስጥ ብታልፍም በተሟላ መልኩ የሽግግር ፍትህ አላባዎች ተተግብረው አያውቁም። በነዚህ የሽግግር ሂደቶች ያለፉ ጉልህ የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶች፣ በደሎች እና ጭቆናዎችን መንስኤ፣ ምንነት፣ አይነት እና የጉዳት መጠን በበቂ መንገድ በማጣራት፣ እውነትን በማውጣት እና እውቅና በመስጠት - በተጠያቂነት፣ በይቅርታ እና በእርቅ ላይ የተመሰረተ የተሟላ ሂደት አልተከናወነም።*

*የደርግ መንግስት የአፄ ኃይለስላሴን መንግስት ከስልጣን ካስወገደ በኋላ - በንጉሱ ሥርዓት ዘመን መጠነ ሰፊ በደል ፈፅመዋል፣ አላግባብ በልጽገዋል እና ለወሎው ረሀብ እልቂት ተጠያቂ ናቸው ያላቸውን መኳንንቶች፣ መሳፍንቶች፣ ሚኒስትሮች እና ሌሎች ባለስልጣናትን አሰሯል። የነዚህን ባልስጣናት ጉዳይ እያጣራ ለፍርድ የሚያቀርብ አጣሪ*



Draft

ኮሚሽንም ተቋቁሞ ነበር። አጣሪ ኮሚሽኑ ምርመራውን ማካሄድ ጀምሮ የነበረ ቢሆንም - ምርመራውን ከማጠናቀቁ በፊት ደርግ ከ50 በላይ በሚሆኑት ባለስልጣናት ላይ የሞት ፍርድ ውሳኔ በማስተላለፍ እርምጃ እንዲወሰድ አድርጓል፡ ፡

በ1983 ዓ.ም. ኢህአዴግ በትረ-መንግስቱን በመቆጣጠር የኢትዮጵያ የሽግግር መንግስት የመሰረተ ሲሆን - በደርግ አስተዳደር ዘመን ለተፈጸሙ ጥሰቶች ምላሽ ለመስጠት የወንጀል ክስ መመስረትን እንደ ዋነኛ መንገድ ተጠቅሟል። በአዋጅ ቁጥር 22/1985 መሰረት ተጠሪነቱ በቀጥታ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ የሆነ ልዩ የዓቃቤ ሕግ ፅህፈት ቤት የተቋቋመ ሲሆን - በስሩም ከ400 በላይ ሰራተኞች ነበሩት። የፅህፈት ቤቱ ዋና ስራም የደርግ ባለስልጣናት የፈጸሟቸውን ወንጀሎች መመርመር፣ ክስ መመስረት እና ማስቀጣት ነበር።

በዚህም መሰረት በተለያዩ ሰዎች ላይ ምርመራዎችን በማጣራት፣ በመደበኛው ፍርድ ቤት ክስ በመመስረት እና በመከራከር ኮሎኔል መንግስቱ ሀይለማርያምን ጨምሮ - በበርካታ ተጠርጣሪዎች ላይ የቅጣት ውሳኔ እንዲሰጥ አድርጓል። በዚህ ሂደት ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ምስክሮች እና የሰነድ ማስረጃዎችን የማደራጀት እና ክስ የመመስረት ስራው ራሱን በቻለ ተቋም እንዲሰራ መደረጉ በጥንካሬ ሊወሰድ የሚገባው ነው። ከዚህም በተጨማሪም በቀጣይ አመታት አዲስ ህገ-መንግስት የማውጣት፣ ዴሞክራሲያ ተቋማትን - ማለትም የሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን እና የህዝብ እንባ ጠባቂ ተቋምን - የማቋቋም ስራ ተሰርቷል።

በዚህ ወቅት የነበረውን የፍትህ ሂደት ከሽግግር ፍትህ ሂደት አላባዎች አንፃር ስንመለከተው የሚከተሉት ጉድለቶች እንደነበሩበት መረዳት ይቻላል፡-

- የፍትህ ሂደቱ መጠነ-ሰፊ የሆነ የወንጀል ክስ በማቅረብ ላይ ብቻ ትኩረት ማድረጉ እና በደርግ ጊዜ የተፈጸመውን ግፍና በደል በበቂ ሁኔታ ለመሸፈንና ለመፍታት የሚያስችሉ እንደ ይቅርታ፣ እርቅ እና እውነትን ማፈላለግ ያሉ ስልቶችን አለመጠቀሙ፤
- በደርግ መንግስት የስልጣን ዘመን በሌሎች አካላት የተፈፀሙ በደሎች እንደነበሩ ቢታወቅም - የክስ ሂደቱ በደርግ ባለስልጣናት ላይ ብቻ ማተኮሩ - በተለይም በሌሎች ሲቪል እና ታጣቂ ቡድኖች ተፈጽመዋል የተባሉ ወንጀሎችን አለማየቱ - የፍትህ ሂደቱን የአሸናፊዎች ፍትህ ተምሳሌት እንዲሆን ማድረጉ፤
- በፍትህ ሂደቱ የነበረው የተጎጂዎች ተሳትፎ ማስረጃ በማቅረብ ላይ ብቻ መገደቡ፣ እንዲሁም የክሱ ሂደትም ቢሆን ከፍትሀብሄር ክስ ጋር ያልተጣመረ እና ማካካሻ የማግኘት መብትን ያስከበረ አለመሆኑ - የድርጊቱ ሰለባዎች እና ተጎጂዎች በቂ ማካካሻ እንዲያገኙ አለማድረጉ - ከሚጠቀሱ ክፍተቶች ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡ ፡

በ2010 ዓ.ም. በሀገራችን የተፈጠረውን የፖለቲካ ለውጥ ተከትሎ - መንግስት ያለፉ ጉልህ የሰብአዊ መብት ጥሰቶች፣ ቁርሾዎች እና በደሎች በእውነት በእርቅ እና በፍትህ ላይ ተመስርቶ ለመፍታት እና የዴሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ መንገዱን ለማመቻቸት - በርካታ የሽግግር ፍትህ እርምጃዎችን ወስዷል። ለደረሱ በደሎች እንደመንግስት በይፋ ይቅርታ የመጠየቅ፣ የእርቀ-ሰላም ኮሚሽን የማቋቋም፣ ክስ፣ ምህረት እና ለሽግግር ፍትህ ሂደት አስተዋፅዎ የሚያደርጉ የህግ እና የተቋማት ማሻሻያ ስራዎች ተከናውነዋል።

ይሁንና የሽግግር ፍትህ አላባዎችን በተሟላ እና ወጥ በሆነ መልኩ ተቀናጅተው የሚተገበሩበት የፖሊሲ አቅጣጫ ባለመኖሩ፣ አንዱ ከሌላው ጋር ያለው መስተጋብርም በግልፅ ባለመደንገጉ፣ እንዲሁም የተወሰዱት እርምጃዎች የየራሳቸው ጉድለቶች ስለነበሩባቸው - የሽግግር ፍትህ ሂደት አላማን ማሳካት አልተቻለም። ከተደረጉት ጥረቶች እና ከነበሩ ጉድለቶች መካከል የሚከተሉትን በማሳያነት ማንሳት ይቻላል፡-

**የወንጀል ክሶችን በሚመለከት፡**

Draft

ጉልህ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች እና ከባድ ሙስና እና/ወይም ሌሎች ከፍተኛ የህዝብ ንብረት ምዝበራ ድርጊቶችን በተመለከተ - በመንግስት ባለስልጣናት ላይ ክስ ቀርቦ ጉዳያቸው በፍርድ ቤት የታየ/በመታየት ላይ ያለ ቢሆንም - ይህ ሂደት ከሽግግር ፍትህ ሂደት ዘዴዎች እና አላባዎች አንፃር የሚከተሉት ዋና ዋና ጉድለቶች ያሉት መሆኑ ተለይቷል።

- ክሶቹ በኢህአዴግ ዘመነ-መንግስት በደረሱ ጠቅላላ ጉልህ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች ላይ ያተኮሩ አለመሆናቸው፣ ክስ ሊቀርብባቸው የሚገቡት ጉዳዮችን በሙሉ ያላካተተና በእጅጉ አናሳ የበዳይ ወሰን ያለው መሆኑ፣
- በአመዛኙ ክሶች የቀረቡት ሊከሰሱ ከሚገባቸው መካከል ማግረጥ በሚመስል መልኩ መሆኑ፣
- ረዥም የፍርድ ሂደት መኖሩ፣ አብዛኛዎቹ ጉዳዮች አሁንም ድረስ ውሳኔ አለማግኘታቸው፣
- የጉዳት ሰለባዎች እና የተጎጂዎች ማካካሻ የማግኘት መብትን ባስከበረ መልኩ የሚካሔድ የክስ ሥርዓት አለመሆኑ፣ ይህም በተጎጂዎችና በህብረተሰቡ የፍትህ መጓደል ስሜት ከመፍጠሩም ባሻገር - ለእርቅ አስተዋፅኦ አድርጓል ለማለት የማያስችል ሂደት መሆኑ፣
- የዜጎችን ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶችን አክብሮ በማስከበር፣ እንዲሁም ያለፉ ጥፋቶች እንዳይደገሙ በማድረግ ረገድ ወሳኝ ሚና ሊጫወቱ የሚችሉ እንደ ፖሊስ፣ ዐቃቤ ሕግ፣ ፍርድ ቤቶች እና በሌሎች የፍትህና ዲሞክራሲ ተቋማት ላይ - ከተወሰነ የአመራር ለውጥ በስተቀር - ይህ ነው የሚባል በማጣራት እና በልየታ ላይ የተመሰረተ የሽግግር ስልትን (vetting) የተገበረ ለውጥ አለመከናወኑ - የሚጠቀሱ ናቸው።

**ምህረትን በሚመለከት፣**

የምህረት አሰጣጥና አፈፃጸም ሥርዓት ወጥነት ስላልነበረው ይህን ለማስተካከል የምህረት አሰጣጥ እና አፈጻጸም ሥነ-ሥርዓት አዋጅ ቁጥር 1089/2010 እንዲወጣ ተደርጓል። ይህን አዋጅ መሰረት አድርጎ በተለያዩ የወንጀል ድርጊቶች ውስጥ ለተሳተፉ ሰዎች ምህረት ለመስጠት የሚያስችል አዋጅ ቁጥር 1096/2010 ወጥቷል። አላማውም በነበረው ፖለቲካዊ አለመረጋጋት ምክንያት በወንጀል የተሳተፉ ሰዎችን ምህረት በመስጠት ሰላምና መረጋጋትን ለማስፈን፣ ብሔራዊ መግባባትን ለመፍጠር እና ይቅር መባባልን ለማበረታታት፣ የፖለቲካ ምህዳሩን ለማስፋት - በተለይም ፖለቲካዊ መብታቸውን ተግባራዊ ለማድረግ በመንቀሳቀሳቸው የወንጀል ተጠያቂነት ስጋት ላደረባቸው ኢትዮጵያዊያንና ትውልደ-ኢትዮጵያዊያን ምህረት በመስጠት ወደ ሀገራቸው እንዲመለሱ ሁኔታዎችን ማመቻቸት በማስፈለጉ እንደሆነ በአዋጁ ላይ ተገልጿል። ይሁንና ይህ ሂደት ከሽግግር ፍትህ ሂደት ዘዴዎች እና አላባዎች አንፃር የሚከተሉት ጉድለቶች ነበሩት።

- የምህረት አሰጣጥ ሂደቱ ወንጀል ፈፃሚ ተብለው በተጠረጠሩ ሰዎች ላይ በ6 ወር ጊዜ ውስጥ ጥያቄ እንዲያቀርቡ ከመጠየቅ ውጪ ምንም አይነት ቅድመ-ሁኔታ ያላስቀመጠ መሆኑ፣ ይህም በሽግግር ፍትህ ሂደት የማይመከረውን አይነት ጠቅላላ ምህረት (blanket amnesty) የሰጠ መሆኑ፣
- የምህረት ሂደቱ ተጎጂዎችን ያላሳተፈ መሆኑ፣ በውስጡም ተጎጂዎችን የመካስ እና ይቅርታ የመጠየቅ ስርዓቶች ያልተካተቱበት መሆኑ፣
- ሰላምና መረጋጋት ከማምጣት አንጻር ከታየ በአዋጁ ተጠቃሚ ሆነው ከእስር የተለቀቁ ሰዎች ባለፉት አራት አመታት በተከሰቱ ግጭቶች ውስጥ ተመልሰው መሳተፋቸው እና በቁጥጥር ስር መዋላቸው ሲታይ ከመፀፀት ጋር በተያያዘ የታለመውን ግብ ያላሳካ መሆኑ፣

Draft

- በምህረት ተጠቃሚ መሆን የሚገባቸው ሰዎች በፌዴራል እና በክልል መዋቅሮች በተዘጋጁ ቢሮዎች በመቅረብ እና በማመልከት የምህረት ምስክር ወረቀት የሚወስዱበት ሥርዓት የተዘረጋ ቢሆንም - አፈፃፀሙ ላይ ጠንከር ያለ ክትትል ባለመደረጉ - የምህረት አሰጣጥ እና አፈፃፀም ሥርዓቱ በአግባቡ አለመከናወኑ፣ የምስክር ወረቀት ያልያዙ ሰዎችም በማናለብኝነት ወደ ማህበረሰቡ መቀላቀላቸው፣ ይህም የመንግስትን ህግ የማስከበር ብቃት ጥያቄ ውስጥ ያስገባው መሆኑ - የሚጠቀሱ ናቸው።

**ተቋማዊ አደረጃጀትን በተመለከተ፣**

ለሀገራችን የመጀመሪያ የሆነዉ የእርቀ-ሰላም ኮሚሽን በአዋጅ ቁጥር 1102/2011 ተቋቁሞ የነበረ ሲሆን፣ ኮሚሽኑም በኢትዮጵያ በተለያዩ ጊዜያት እና በተደጋጋሚ የተፈጸሙ ጉልህ የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶችን፣ በደሎችን፣ ቁርሾዎችን እና ዝንፈቶችን በበቂ ደረጃ ለይቶና አጣርቶ እውቅና በመስጠት - በእውነት፣ እርቅ እና ፍትህ ላይ የተመሰረተ ዘላቂ ሰላም እና ዲሞክራሲያዊ ስርአትን ለመገንባት አስተዋጾ እንዲያደርግ ስልጣን እና ሀላፊነት ተሰጥቶታል። ይሁንና ተቋሙ ከተመሰረተበት ጊዜ ጀምሮ የዝግጅት ሥራዎችን ሲያከናውን ቆይቶ ዋና ተግባሩን መፈፀም ሳይጀምር እና ተጨባጭ ውጤት ሳያስገኝ - የተሰጠው የሶስት አመት የስራ ዘመን የካቲት 2014 ዓ.ም በማብቃቱ እንዲፈርስ ተደርጓል። ኮሚሽኑ ከሽግግር ፍትህ አንፃር የተጣለበትን ዓላማ ማሳካት ላለመቻሉ የሚከተሉትን ምክንያቶች በማሳያነት መጥቀስ ይቻላል።

- የኮሚሽኑ የምስረታ ሂደት ትርጉም ያለው እና ሀገር-አቀፍ የህዝብ ምክክር ያልተደረገበት መሆኑ፣ በረቂቁ ላይ ከሚመለከታቸው አካላትና ባለሙያዎች ጋር ምክክር አለመደረጉና ግብአት አለመወሰዱ፣
- ለኮሚሽኑ የተሰጠው ተግባርና ኃላፊነት ግልፅነት የጎደለውና ተግባራዊ ለማድረግ አስቸጋሪ መሆኑ፣ ተግባርና ኃላፊነቱ ከሌሎች የሽግግር ፍትህ ሂደቶች ጋር የነበረው መስተጋብር እና የመመጋገብ ግንኙነት በግልፅ አለመቀመጡ፣ ኮሚሽኑ ይቅርታ እና ምህረት እንዲሰጥ ስልጣን ያልተሰጠው መሆኑ፣
- የኮሚሽኑ ኮሚሽነሮች ሲመረጡ እና ሲሾሙ ቀጥተኛ የህዝብ ጥቆማ፣ ውይይት እና ተሳትፎ ያልነበረ መሆኑ፣ ይህም በኮሚሽኑ ቅቡልነት ላይ አሉታዊ አስተዋጽዎ ማድረጉ፣
- በፖለቲካ እንቅስቃሴ ውስጥ የነበሩ እንዲሁም ገለልተኝነታቸው ጥያቄ ውስጥ የሚገባ - በዳይ ወይም ተበዳይ ናቸው ተብለው የሚታሰቡ ግለሰቦች ኮሚሽነር ሆነው መሾማቸው፣
- ለዚህ ከፍተኛ ሀላፊነት የሚሰየሙ ኮሚሽነሮች የሙሉ ሰአት ሰራተኞች አለመሆናቸው፣ ቁጥራቸውም ከተለመደው እጅግ የበዛ (41 የሚጠጋ) መሆኑ፣[3]
- ኮሚሽኑ የሚያጣራቸው ያለፉ ጉልህ የሰብአዊ መብት ጥሰቶች ከየትኛዉ ጊዜ እንደሚጀመር አለመቀመጡ፣
- ተቋሙ ከሚችለዉ በላይ ሀላፊነት የተሰጠው መሆኑ (ለምሳሌ አሁናዊ ግጭት መፍታት ላይ የሚሰሩ እና እንዲሰሩ ሀላፊነት የተሰጣቸው መንግስታዊ ተቋማት እያሉ - ይህንን ተግባር ጊዜያዊ ለሆነዉ የእርቀ-ሰላም ኮሚሽን ተጨማሪ ተግባር እንዲሆን መደረጉ፣ ሀገራዊ ምክክር የማድረግ ተጨማሪ ተግባር የተሰጠው መሆኑ፣ እንደ እርቀ-ሰላም ያሉ ኮሚሽኖች ግጭት መፍታት እና ሀገራዊ ምክክርን ማካሄድ ዋና ተግባራቸው እንዲያደርጉ በማይመከርበት ሁኔታ ይህ መፈፀሙ።

[3] የሌሎች ውጤታማ የሚባሉ የእውነት ኮሚሽኖች ከፍተኛው የኮሚሽነሮች ብዛት ከ25 አይበልጥም።

በአጠቃላይ ሀገራችን በነበሩት የሽግግር አጋጣሚዎች - የሽግግር ፍትህ ሂደት አላባዎችን ለማሳካትም ሆነ ፍትህን ለማረጋገጥ ውሱን ሙከራዎች እንደነበሩና በዚህም የተገኙ ልምዶችና ውጤቶች እንዳሉ መመልከት ይቻላል። ይሁንና ከ2010 ዓ.ም በኋላ የተከናወኑትን ጨምሮ - በኢትዮጵያ የተደረጉ የሽግግር ፍትህ ሙከራዎች ያልተሟሉ እና በቂ ባልሆኑ ሂደቶች የተተገበሩ እንደነበሩ ተስተውሏል። በተሟላ መልኩ - የሽግግር ፍትህ ሂደት አላባዎችን እና ዘዴዎችን አካትተው፣ በተቀናጀ ሁኔታ ባለመተግበራቸውም - ስኬታማ መሆን አልቻሉም። በመሆኑም - ካለፈው አስከፊ ሁኔታ በመማር ወደ ፊት ለመራመድ - የሽግግር ፍትህ ሂደቶች የሚፈጥሯቸውን አጋጣሚዎች እንዳንጠቀም ምክንያት ሆነዋል። ይህም በራሱ እስካሁን ድረስ ለቀጠለው ግጭት፣ የእርስ በእርስ ጦርነት እና የሰብአዊ መብት ጥሰቶች መንስኤ የሆኑ በርካታ ጉዳዮች ሳይፈቱ እንዲቀጥሉ አስተዋፅዎ አድርጓል።

## 1.3. በኢትዮጵያ የሽግግር ፍትህ አስፈላጊነት

ከላይ ለማሳየት እንደተሞከረው በ2010 ዓ.ም የመጣውን ለውጥ ጨምሮ - በኢትዮጵያ የተሞከሩት የሽግግር ፍትህ አላባዎች የታለመላቸውን አላማ ማሳካት አልቻሉም። ስለሆነም በተሟላ እና በተቀናጀ መልኩ የሚዘረጋ፣ አሳታፊ የሆነ፣ ተጎጂዎችን ማእከል ያደረገ፣ የዓለም-አቀፍ የሰብአዊ መብት መርሆችንና ድንጋጌዎችን ያከበረ፣ በሌሎች ሀገራት እና በሀገራችን ከነበሩ ልምዶች ትምህርት የሚወስድ፣ የሀገራችንን ፖለቲካዊ እና ማህበራዊ አውድ ግንዛቤ ውስጥ የሚያስገባ - የሽግግር ፍትህ ሂደት በመቀመር እና በግልፅ የፖሊሲ ማዕቀፍ እንዲመራ በማስቻል - ተግባራዊ ማድረግ እጅግ አስፈላጊ ነው። ለዚህም የሚከተሉትን ምክንያቶች በማሳየት ማንሳት ይቻላል፡-

### ሀ) የሀገራዊ አውዱ ሁኔታ የተሟላ የሽግግር ፍትህ ስርዓት ሂደትን መተግበር አስፈላጊ እንደሆነ የሚያመላክት መሆኑ፣

በኢትዮጵያ ጉልህ የሰብአዊ መብት ጥሰቶች ስልታዊና መጠነ-ሰፊ በሆነ ሁኔታ ሲፈጸሙ የነበረ ስለመሆኑ በርካታ ሪፖርቶች ያመለክታሉ። ከ 2010 ዓ.ም ጀምሮ በርካታ የፍትህ ማሻሻያ ስራዎች ቢሰሩም - የሰብአዊ መብት ጥሰቶች፣ አለመረጋጋት፣ ግጭቶች እና የእርስ-በርስ ጦርነት በመቀጠሉ አሁንም ዜጎች ለሞት፣ ለስደትና ለንብረት ውድመት እየተጋለጡ ይገኛሉ። ከዚህ የጥፋት አዙሪት እንዳንወጣ ካደረጉ ምክንያቶች መካከል - በሀገራችን የነበሩ የተደራረቡ በደሎች፣ የመብት ጥሰቶች፣ የተዛነፉ የታሪክ አረዳዶች፣ ለእነዚህ ጥሰቶች የተሰጡ ምላሾች ምሉዕ አለመሆን፣ በዜጎች ላይ ለተፈፀሙ ጥሰቶች ፍትህ አለማግኘት፣ ተጎጂዎች አለመካሳቸው፣ እና ሀገራዊ እርቅ አለመከናወኑ ተጠቃሽ ናቸው።

የአጥፊዎች እና የተጎጂዎች ብዛት፣ የበደሎች መደራረብ፣ እና የጥፋቶች ማህበረሰባዊ ቅርፅ መያዝ - ህዝቡ ለፍትህ ተቋማት ካለው ያነሰ ቅቡልነት ጋር ተዳምሮ - በመደበኛው የፍትህ ሥርዓት እና አካሄድ ለሁኔታዎች ፍትህ መስጠትም ሆነ ይቅርታና እርቅ ማከናወን እንዳይቻል አድርጎታል። ስለሆነም የሀገሪቱን አሁናዊ ሁኔታ ግንዛቤ ውስጥ ያስገባ፣ ያለፈውን በአግባቡ የሚያስተናግድ፣ ለነገም መሰረት ለመጣል የሚያስችል፣ በዓለም-አቀፍ እና ሀገራዊ ልምዶች የተቀመረ፣ እንዲሁም በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች የተለያዩ አጀንዳዎችን ይዘውና ነፍጥ አንግበው የሚታገሉ ቡድኖችን ትጥቅ አስፈትቶ ከማህበረሰቡ ጋር እንዲቀላቀሉ የሚያደርግ - የተሟላ የሽግግር ፍትህ ሂደት መተግበር የግድ ይላል። ይህ አይነቱ አካሄድ - ሀገሪቱ ካሉባት ውስብስብ ችግሮች አዙሪት እንድትወጣ ከፍተኛ አስተዋፅዎ ያደርጋል።

### ለ) የተሳካ የሽግግር ፍትህ ሂደት ለሀገረ-መንግስቱ ግንባታ እና ቀጣይነት የሚኖረው ሚና ከፍ ያለ መሆኑ፣

በሀገራችን ከነበረው የጥፋት አዙሪት ለመውጣት እና ለተፈጠሩ ጥሰቶች አግባብ ያለው ምላሽ ለመስጠት በእውነት፣ በፍትህ፣ በሰላም እና በእርቅ ላይ በመመስረት ማህበራዊ ግንኙነቶችን ማደስ እጅግ አስፈላጊ ነው። በታሪክ ኢትዮጵያ እውነተኛ የእርቅ ሂደትን አድርጋ የምታውቅበት ወቅት ወይም አጋጣሚ የለም። ይልቁንም በአንዳንድ ዘመናት ስልጣን ላይ የነበሩ መንግስታት የያዙት አቋም "የተጣላ የለም፤ እርቅ አያስፈልገንም" የሚል ይዘት የነበረው እንደሆነ ይታወቃል። በዚህም ምክንያት - በሀገሪቱ በተለያዩ ጊዜያት የተፈጸሙ ጉልህ የሰብአዊ መብት ጥሰቶች እና ቁርሾዎች - አግባብነት ባለው መልኩ ሳይፈቱ እየተንከባለሉ እዚህ ዘመን ላይ ደርሰዋል።

Draft

ስለሆነም ያለፉ በደሎችን አንስቶ መወያየት ፈታኝ ቢሆንም - ይቅር መባባልና እርቅ እንዲኖር ማድረግ ለሀገረ-መንግስቱ ግንባታ መሰረታዊ ጉዳይ ነው። በሀገሪቱ የነበሩና የቀጠሉ ውስብስብ ችግሮች ዘላቂ መፍትሄ ካልተበጀላቸው ታሪካዊ ኢ-ፍትሃዊነትን የሚያሳዩ ተፃራሪ ትረካዎች - ህብረተሰቡን በተለያየ መንገድ ማቁሰላቸውን እንዲቀጥሉ ያደርጋል። በመሆኑም ሀገሪቱ - የተከፋፈለውን ህዝብ ለማቀራረብ፡ የሻከረውን ግንኙነት ለመጠገን፡ ተጠያቂነትን ለማረጋገጥ እና እርቅ ለመፍጠር - የሽግግር ፍትህ ዘዴዎችን መጠቀም እንደ አማራጭ መውሰድ ይኖርባታል። በዚህ ሂደት - ላለፈው ቁስል እውቅና ለመስጠት፡ የሰውን ክብር ለመመለስ፡ ለጋራ ዳግም ውህደት እና ለሀገር ግንባታ - የሽግግር ፍትህ የሚኖረው ሚና እጅግ ወሳኝ ነው።

### ሐ) የተሳካ የሽግግር ፍትህ ሂደት ሳይተገበር የዲሞክራሲ ሽግግርም ሆነ ዘላቂ ሰላም ማረጋገጥ የማይቻል መሆኑ።

በተለያዩ ሀገሮች እንደታየው - ያለፉ በደሎችን እና ጉልህ የሰብአዊ መብት ጥሰቶችን በአግባቡ ሳይፈቱ፡ ሙሉ እውነትን ሳያወጡ፡ ተጠያቂነትን ሳያሰፍኑ፡ እና እውቅና ሳይሰጡ - በእርቅ፡ በሰላም እና በፍትህ ላይ የተመሰረተ የተሳካ ዲሞክራሲያዊ ሽግግር ማድረግ አዳጋች ነው። በዚህም ምክንያት በሀገራችን በተለያዩ ጊዜያት የተፈጸሙ ጉልህ የመብት ጥሰቶች እና ቁርሾዎች አግባብነት ባለው መልኩ ሳይፈቱ ሲንከባለሉ የመጡ እንደመሆኑ መጠን - በደሎቹ እንዲሽሩ፡ ቁርሾዎች እንዲጠገኑ፡ ወደ ዲሞክራሲ የሚደረገው ሽግግር እንዲሳካ፡ እንዲሁም ዘላቂ ሰላም ማረጋገጥ እንዲቻል - የተሟላ የሽግግር ፍትህ ሂደት መተግበር ጠቃሚ ብቻ ሳይሆን እጅግ አስፈላጊ ነው።

### መ) የሽግግር ፍትህ ሥርዓት መተግበር ለሰብአዊ መብት መከበር እና ለህግ የበላይነት መረጋገጥ የሚኖረው አስተዋጽኦ የማይተካ መሆኑ፡

በሀገራችን ሰፊ የሰብአዊ መብት ጥሰት የተፈፀመ ቢሆንም - ሁሉንም አጥፊዎች እንደየጥፋታቸው ያለምንም ወጣ ገባነት ተጠያቂ የሚያደርግ ሥርዓት አለመኖሩ - ጥሰቶቹ ተደጋግመው ለመከሰታቸው አንዱ ምክንያት ሆኗል። እነዚህ ጥሰቶች በአብዛኛው የተፈፀሙት ምንም አይነት የፖለቲካ ተሳትፎ በሌላቸው፡ ስለነገሩም ምንም ግንዛቤ ባልያዙ ኢትዮጵያውን ላይ ነው። ድርጊቶቹ እንዳይፈፀሙ የመቆጣጠር ወይም የመከላከል ኃላፊነት ያለባቸው የመንግስት ሀላፊዎች እና የማህበረሰብ ልሂቃኖችም - ነገሮች እንዲባባሱ ጉልህ አስተዋፅኦ ሲያደርጉ ታይተዋል።

እነዚህ ድርጊቶች ተደጋግመው ስለሚፈፀሙ እና ከተፈፀሙ በኋላም ምርመራው ይሁን የክስ ሂደቱ ተጎጂዎችን ያላማከለ እና በህብረተሰቡም እምነት የተጣለበት ባለመሆኑ - በሂደት ህዝቡ በፍትህ ሥርዓቱ ላይ ያለው እምነት አናሳ እንዲሆን አድርጎታል። ስለሆነም ሁሉን-አቀፍ የሽግግር ፍትህ ሥርዓትን ተግባራዊ ማድረግ - ተቀባይነት ያለው የክስ ሂደትን እንዲኖር፡ ለሰብአዊ መብት ጥሰቶች ተገቢ ትኩረት እንዲሰጥ፡ የተጠያቂነት ሥርዓት እንዲጠናከር፡ ተጎጂዎችን ማእከል ያደረገ የይቅርታ፡ እርቅ እና ማካካሻ ስርአት እንዲኖር በማድረግ - ለሰብአዊ መብቶች ባህል መዳበር እና ለህግ የበላይነት መረጋገጥ መሰረት ይጥላል።

## ክፍል ሁለት

## የሽግግር ፍትህ ስልቶች እና የፖሊሲ አቅጣጫ አማራጮች

### 2.1. መግቢያ

የሽግግር ፍትህ ሂደት ክስን፡ እርቅን፡ ምህረትን፡ እውነትን፡ ማካካሻን፡ ተቋማዊ ማሻሻያን እና ሌሎች ተገቢነት ያላቸው የሽግግር ፍትህ አላባዎችን በአንድነትና በተመጋጋቢነት ያካተተ ሁለንተናዊ አካሄድ ነው። እነዚህ ስልቶች የሀገራትን ነባራዊ ሁኔታ ከግምት ውስጥ በማስገባት እና ተገቢ ተቋማዊ አደረጃጀትን በመጠቀም ሲተገበሩ የበለጠ ውጤታማ ይሆናሉ።

ማናቸውም አገር ተግባራዊ የሚያደርገው የሽግግር ፍትህ የሚተገበርባቸው አማራጮች እና መንገዶች - የአገሩን ታሪካዊ፡ ኢኮኖሚያዊ፡ ማህበረሰባዊ እና ፖለቲካዊ አውድ - እንዲሁም በሽግግር ሂደቱ ባህሪ ላይ ተመስርቶ ሊወሰን ይገባል። ኢትዮጵያ አሁን በሽግግር ሂደት ውስጥ ያለች ሀገር እንደመሆኗ መጠን - የሽግግር ፍትህን ተግባራዊ



Draft

ማድረግ የሚገባት ስለመሆኑ በክፍል አንድ የተመለከተ ሲሆን - የትኛውን የሽግግር ፍትህ መጠቀም አለባት የሚለው ጉዳይ በጥንቃቄ አይቶ መምረጥ እና መወሰን አስፈላጊ ይሆናል። በተጨማሪም የትኞቹን የሽግግር ፍትህ ስልቶች ለየትኞቹ ጉዳዮች መጠቀም ሽግግሩን ውጤታማ ያደርገዋል የሚለው ጉዳይም ውሳኔ የሚፈልግ ነው።

ስለሆነም በዚህ ክፍል - በሀገራችን ሊተገበር ከሚችሉ የሽግግር ፍትህ አላባዎች ውስጥ - ካለንበት ነባራዊ ሁኔታ አንፃር አቅጣጫ ሊቀመጥባቸው የሚገቡ ጉዳዮችን እና ሊተገበሩ የሚችሉ የፖሊሲ አማራጮችን በመለየት - እንደሚከተለው ቀርበዋል።

## 2.2. ክስ

### 2.2.1. ጠቅላላ

በሽግግር ፍትህ ሂደት መተግበር ከሚኖርባቸው ስልቶች አንዱ የወንጀል ምርመራ በማድረግና ክስ በመመስረት ጥፋት ፈፃሚዎች የሚቀጡበትን ሂደት መዘርጋት ነው። በሽግግር ፍትህ ሂደት የወንጀል ክስ ተገቢ ተደርጎ የሚወሰደው በዓለም-አቀፍ የሰብአዊ መብት ሰነዶች በሀገራት ላይ ከተጣሉ ግዴታዎች ውስጥ አንዱ ሰብዓዊ መብቶችን የመጠበቅ ግዴታ (duty to protect) በመሆኑ ነው። ይህም በተለይ የመክሰስ ግዴታን የሚያካትት ነው። በተጨማሪም ጉልህ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች ሲፈፀሙ - መንግስት ተጠያቂነትን የማስፈን ግዴታ ያለበት ስለመሆኑ በአለም-አቀፍ ደረጃ የወጡ ስምምነቶች - ለምሳሌ የጄኔቫ ኮንቬንሽን፣ የዘር ማጥፋትን የሚመለከተው ኮንቬንሽን፣ እና ድብደባና ሌሎች ጉልህ ኢሰብዓዊ ድርጊቶችን ለመከላከል የወጣው ኮንቬንሽን - በግልጽ ያመለክታሉ። እንዲሁም የአፍሪካ የሽግግር ፍትህ ፖሊሲ ለተወሰኑ የወንጀል ድርጊቶች የመክሰስ ግዴታን ያስቀምጣል።

በመሆኑም ክስ በመመስረት ይህን ሀላፊነት መወጣት - ሀገሪቱ ዓለማቀፍ ግዴታን ለመወጣት ያላትን ቁርጠኝነት እና ለሰብዓዊ መብቶች መከበር ያላትን ቃልኪዳን የሚያመለክት በመሆኑ፣ ፍትህ የማግኘት መብትንም ስለሚያረጋግጥ፣ በጥፋተኞች መካከል ግለሰባዊ ሀላፊነትን ስለሚያስከትል፣ በተደጋጋሚ ከሚያጋጥም የጅምላ ፍረጃ የሚጠብቅ በመሆኑ፣ የህግ የበላይነት እና ተጠያቂነት እንዲኖር ስለሚያደርግ፣ ተመሳሳይ ክስተቶች እንዳይደገሙ ስለሚከላከል፣ በተጓዳኝም እውነቱን በመግለፅ እርቅን ሰላምን እና ዲሞክራሲን ስለሚያበረታታ - በኢትዮጵያ ተግባራዊ ከሚደረጉ የሽግግር ፍትህ ሂደት ስልቶች አንዱ መሆን ይኖርበታል።

### 2.2.2. የትኞቹ ጉዳዮች ያስከስሳሉ?

በሽግግር ፍትህ ማእቀፍ የሚከናወን የወንጀል ክስ - አለም-አቀፍ እና ሌሎች ከባድ ወንጀሎችን ብቻ የሚመለከት ነው። የወንጀል አይነቶቹን በሚመለከት የክስ ፍትህ ሂደቱን ትክክለኛ ወሰን ማስቀመጥ አስፈላጊ ነው። በዚህ ረገድ የሚከተሉትን አማራጮች ማየት ይገባል።

**አማራጭ አንድ፦ ጉልህ በሆኑ የሰብአዊ መብት ጥሰቶች ወይም ከባድ ወንጀሎች ላይ ያተኮረ የክስ ሂደት ማከናወን፣**

በሽግግር ፍትህ ሂደት - ክስ - አንድ የፍትህ መንገድ እንጂ ብቸኛው መንገድ አለመሆኑን ግምት ውስጥ ማስገባት ያስፈልጋል። በመሆኑም የወንጀል ምርመራ እና ክሶች የሚከናወኑት በሁሉም የሰብአዊ መብት ጥሰት ወንጀሎች ላይ ሳይሆን - ዋና ዋና በሚባሉ - ዓለምአቀፋዊ የጥፋት ባህርይ ባላቸው የወንጀል ዓይነቶች እና ሌሎች ከባድ ወንጀል ተብለው በወንጀል ህግ በተለዩ ድርጊቶች ላይ ብቻ ነው። በዚህ አማራጭ ውስጥ የሚካተቱ የወንጀል ድርጊት አይነቶች በስብዕና ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች፣ የዘር ማጥፋት ወንጀሎች፣ የጦር ወንጀሎች፣ በሰዎች ላይ እና ንብረት ላይ የተፈጸሙ ሌሎች ከባድ ወንጀሎች እና የመሳሰሉት ናቸው።

**ጠንካራ ጎኖች**

- የክስ ሂደቱ ትኩረት በተወሰኑ ዋና ዋና ወንጀሎች ላይ ብቻ በመሆኑ ሌሎች የሽግግር ፍትህ ስልቶች ተግባራዊ እንዲደረጉ እድል ይሰጣል፣

- በክስ ሂደቱ የሚሸፈኑ የወንጀል አይነቶች አነስተኛ በመሆናቸው የተፋጠነ እና የተቀላጠፈ የፍትህ ሂደት እንዲኖር ያስችላል፡ ጉዳዩን በአጭር ጊዜ ውስጥ ለማጠናቀቅም እድል ይሰጣል፡
- በግፍና በጭካኔ በተፈጸሙ፡ ዓለምአቀፍ ባህርይ ባላቸው እና ከባድ ወንጀሎች ላይ በማተኮር ስራው የበደሎቹን ግዝፈትና አይነት በሚያሳይ መልኩ እንዲከናወን አስተዋፅኦ ያደርጋል፡
- በአለምአቀፍ የሰብአዊ መብት ወንጀሎች ጉዳይ ተጠያቂነትን በማስፈን ረገድ ልምድ ከማስገኘቱም ባሻገር፡ ሀገራት የተጣለባቸውን የመክሰስ ግዴታ በመወጣት አለምአቀፍ ተቀባይነት እንዲኖር ያስችላል።

*ሥጋቶች*

- ድርጊቶቹ የተወሳሰቡ እና ዓለምአቀፍ ባህርይ ያላቸው የወንጀል አይነቶችን የሚመለከቱ በመሆኑ በትክክል ምርመራ ለማካሄድ እና ማስረጃ ለማግኘት ችግር ሊያጋጥም ይችላል፡
- የሚቀርበው የወንጀል ክስ ይዘት/መጠን ውስን ስለሚሆን ሁሉንም ተበዳዮች ላያረካ ይችላል፡
- በሀገራችን እነዚህን ወንጀሎች የሚተረጉም/የሚያቋቁም የተሟላ የህግ ማዕቀፍ አለመኖሩ ተግዳሮት ሊፈጥር ይችላል።

**አማራጭ ሁለት፦ ሁሉንም አይነት የሰብዓዊ መብት ጥሰቶችን ያካተተ የክስ ሂደት ማከናወን**

ከፍተኛ የሰብአዊ መብት ጥሰቶች ወይም ዓለምአቀፍ ባህርይ ያላቸው ወንጀሎችን ለማስረዳት የሚያስፈልጉ ማስረጃዎች በቀላሉ አይገኙም። እንዲሁም ወንጀሎቹ መፈጸማቸውን ለማረጋገጥ የሚያስፈልጉ የወንጀል ፍሬ ነገሮች መሟላት አለመሟላታቸውን ማረጋገጥ አድካሚ እና አስቸጋሪ መሆኑ አይቀርም። በተጨማሪም በነዚህ ወንጀሎች ውስጥ ተሳትፈዋል የሚባሉ ተጠርጣሪዎችን ብቻ ተጠያቂ ማድረግ ከተጎጂዎች አንፃር ሲታይ የራሱ ቅሬታን ይፈጥራል። ስለሆነም በነዚህ ወንጀሎች ብቻ ሳይገደብ - የወንጀል አይነቶቹን ሰፋ አድርጎ የምርመራ እና ክስ ስራዎችን በመስራት - ለተጎጂዎች የፍትህ ጥያቄ ምላሽ በሚሰጥ መልኩ ስራውን ማከናወን አስፈላጊ ይሆናል።

*ጠንካራ ጎኖች*

- በበርካታ የወንጀል ድርጊቶች የተሳተፉ ብዙ ቁጥር ያላቸው ተጠርጣሪዎችን ስለሚያካትት ተጠያቂነት በተሻለ ደረጃ እንዲረጋገጥ ያስችላል፡
- የተበዳዮችን የፍትህ ፍላጎት በተሻለ መልኩ ሊያረካ ይችላል፡
- በመብት ጥሰቶች መካከል ማበላለጥ እንዳይኖር እና በድጋሚ ወንጀሎቹ እንዳይፈፀሙ የተሻለ ወንጀልን የመከላከል ሚና ይጫወታል።

*ሥጋቶች*

- የምርመራ እና ክስ ስራ የሚከናወንባቸው የወንጀል አይነቶች እና ተጠርጣሪዎች በርከት ያለ ቁጥር ሊኖራቸው ስለሚችል የሽግግር ጊዜው የክስ ሂደት ሊሸከም ከሚችለው በላይ ጫና ሊያሳድርበት ይችላል፡
- የሚቀርቡ ክሶች በትልልቅ የሰብአዊ መብት ጥሰቶች ላይ ያተኮሩ ስለማይሆኑ የበደሎቹን ግዝፈትና አይነት በመፈለገው መጠን የሚያሳዩ ያለመሆን እድላቸው የሰፋ ነው፡
- በትልልቅ የወንጀል ድርጊቶች ላይ ትኩረት እንዳይኖር በማድረግ ዓለምአቀፍ ባህርይ ያላቸው የወንጀል ድርጊቶች ክስ እና ምርመራ ስራዎች ተገቢ ሽፋን እንዳይሰጣቸው ያደርጋል፡

- የፍርድ ቤቶችን የስራ ጫና ይጨምራል፡ የሀገሪቱ ውስን ሀብት መጠነ-ሰፊ ለሆኑ ጥሰቶች ምርመራ እና ክስ ስራ እንዲውል ሊያስገድድ ይችላል፡
- ከጉዳዮቹ ስፋት አንፃር በአጭር ጊዜ ውስጥ እልባት መስጠት አያስችልም፡ በዚህም በተጎጂዎች እና በማህበረሰቡ ዘንድ በሂደቱ የመሰላቸት እና ያለመርካት ስጋት ያስነሳል፡
- ሁሉንም የሰብአዊ መብት ጥሰቶች በክስ ሂደት እንዲያልፉ ማድረግ ሌሎች ጠቃሚ የሽግግር ፍትህ ስልቶችን ተግባራዊ ለማድረግ አስቸጋሪ ያደርገዋል።

### 2.2.3. በየትኞቹ አጥፊዎች ላይ ክስ ይመሰረታል?

የወንጀል ክስ መቅረብ የሚገባው - የአሸናፊዎች ፍትህ ተምሳሌትን በማስወገድ - በመንግስት አካላት፡ በታጠቁ ቡድኖች አባላት፡ ወይም በሌሎች ጉልህ የሰብዓዊ መብት ጥሰት በፈፀሙ ግለሰቦች ላይ ሁሉ ሊሆን ይገባል። ይሁንና ከላይ እንደተመለከተው - የሽግግር ፍትህ ሂደቱ አንደኛው መሰረታዊ እሳቤ - በነበሩት ውስብስብ እና ከፍተኛ ጥሰቶች ምክንያት ሁሉንም ተጠርጣሪዎች በወንጀል ክስ እንዲያልፉ ማድረግ የማይቻል ወይም የማይፈለግ መሆኑ ነው። በዚህ መሰረት በተመሳሳይ የወንጀል ድርጊት ውስጥ ቢሳተፉም - የተወሰኑ በወንጀል ክስ ሂደት እንዲያልፉ ሲደረግ፡ ሌሎች ደግሞ በይቅርታ፡ እውነት፡ ምህረት እና በመሳሰሉ የሽግግር ፍትህ ስልቶች እንዲያልፉ ይደረጋል። በዚህ ረገድ ጥያቄ ሆኖ የሚነሳው ዋና ጉዳይ ክስ ሊመሰረትባቸው የሚገቡ ሰዎች - 'ከፍተኛ ተጠያቂ' ናቸው ተብለው በሚታሰቡት ላይ ብቻ ነው ወይስ 'በሌሎቹ ፈጻሚዎች' ላይ ጭምር ነው የሚለው ነው።

**አማራጭ አንድ፦ በወንጀል ክስ ሂደቱ ዋና ጥፋት ፈፃሚዎችን፡ ትእዛዝ የሰጡ፡ ያቀዱ የመሩ እና ከፍተኛ ሀላፊነት ኖሮባቸው ሀላፊነታቸውን ባለመወጣታቸው ምክንያት ጉዳት እንዲደርስ ያደረጉ ግለሰቦች ላይ ብቻ ትኩረት አድርጎ ክስ እንዲመሰረት ማድረግ፡**

በዚህ መልኩ የሚለዩ ግለሰቦች በእውነት፡ በይቅርታ እና በምህረት ሂደቶች ውስጥ የሚሳተፉ ቢሆን እንኳን - ቅጣት ማቅለያ ይሆናቸዋል እንጂ ከወንጀል ክስ ፍትህ ሂደቱ ነፃ አይደረጉም። በሌላ መልኩ በዋና ወንጀል አድራጊነት ሳይሆን በሌላ መንገድ ዋና ተዋናይ ሳይሆኑ በድርጊቱ የተሳተፉ ግለሰቦች - በተበዳዮች ላይ የፈፀሙትን ድርጊት አምነውና ተፀፅተው ከመጡ እና ተበዳዮችን ይቅርታ የሚጠይቁ ከሆነ - በወንጀል ክስ ሂደቱ የሚካተቱ አይሆኑም።

በነዚህ የወንጀል ድርጊቶች የተሳተፉ ሰዎችን በሙሉ ወደ ክስ ስርዓት እናስገባ ከተባለ - የተጠርጣሪዎች ቁጥር በጣም ከፍተኛ ስለሚሆን - የክስ ስራውን ከፍተኛ ተሳትፎ በነበራቸው ተጠርጣሪዎች ላይ ብቻ ተኩረት አድርጎ እንዲከናወን ማድረግ ያስፈልጋል። ነገር ግን ተጠርጣሪዎችን በዚህ መልኩ ለመከፋፈል እንዲቻል ግልፅ የሆነ ስርዓት ሊዘረጋ ይገባል።

**ጠንካራ ጎኖች**

- በዋና ወንጀል አድራጊዎች ላይ ብቻ ትኩረት ስለሚደረግ የምርመራ እና የክስ ስራ በሚሰሩ አካላት ላይ ከፍተኛ የስራ ጫና እንዳይኖር ያግዛል፡
- በድርጊቱ ዋና ተዋናይ ያልሆኑ ሰዎች በሌሎች የሽግግር ፍትህ ስልቶች እንዲያልፉ ስለሚደረግ ለዘላቂ ሰላም እና እርቅ አስተዋፅኦ ያላቸው ሌሎች የሽግግር ፍትህ አማራጮች እንዲተገበሩ ቦታ ይሰጣል፡
- የፍርድ ቤቶችን የስራ ጫና በመቀነስ የሀገሪቱ ውስን ሀብት በከባድ ጥሰት ፈፃሚዎች ላይ ትኩረት እንዲሰጥ ያደርጋል፡
- የክስ ሂደቱ በተወሰኑ የአጥፊ ጎራዎች፡ ቡድኖች፡ ወይም ግለሰቦች ላይ ሳያተኩር - ሁሉን ከፍተኛ ተጠርጣሪዎችን በተገቢ መንገድ በመክሰስ ሽግግሩ በተጠያቂነት ላይ የተመሰረተ እንዲሆን ይረዳል።

Draft

*ሥጋቶች*

- *በተመሳሳይ የወንጀል ድርጊት የተጠረጠሩ ሰዎች በተሳትፏቸው መለያየት ምክንያት ብቻ በተለያየ የሽግግር ፍትህ ስልት እንዲያልፉ መደረጉ በግል ተበዳዮችና በማህበረሰቡ ዘንድ ቅሬታን ሊፈጥር ይችላል፡*
- *የአንዳንድ ጥፋቶች ፈፃሚዎች በዚህ ሂደት አለመካተት - በቀጣይ በሚከሰት የሰብዓዊ መብት ጥሰት ፈፃሚዎቹን ድጋሚ ወንጀል እንዲፈፅሙ ሊያበረታታ ይችላል፡*
- *ዝቅተኛ ተሳትፎ ያላቸውን ሰዎች የመለየት ሂደት ለአድሎ እና ተገቢ ላልሆነ አሰራር በር ሊከፍት ይችላል፡ ፡*

***አማራጭ ሁለት፡- የወንጀል ክስ ሂደቱን በማንኛውም ደረጃ በጉልህ የሰብአዊ መብት ጥሰት የተሳተፉ ሰዎችን በማካተት እንዲከናወን ማድረግ***

*ይህ ሂደት በድርጊቱ በማናቸውም ደረጃ የተሳተፉ ሰዎች ወደ ክስ ስርዓት የሚመጡበት አሰራር ነው። ይሁንና የሽግግር ፍትህ ሂደት እስከሆነ ድረስ ጥፋት ፈፃሚዎች የፈፀሙትን ድርጊት አምነውና ተፀፅተው ተበዳዮችንም ይቅርታ ጠይቀው የሚቀርቡ ከሆነ - የወንጀል ጥፋተኝነት እና/ወይም የክስ ድርድር በማድረግ ቅጣት ማቅለል እና/ወይም አማራጭ ቅጣቶች እንዲፈፀምባቸው ወይም የይቅርታ ተጠቃሚ እንዲሆኑ መደረግ ይኖርበታል።*

*ጠንካራ ጎኖች*

- *ሁሉም ተጠርጣሪዎች በተመሳሳይ ሂደት የሚያልፉ በመሆኑ በሂደቱ ላይ ቅሬታዎች እንዳይነሱ ያደርጋል፡*
- *በደል የደረሰባቸው ሰዎች የፍትህ ፍላጎት በተሻለ መልኩ እንዲሟላ እድል ይሰጣል።*

*ሥጋቶች*

- *ከክስ ውጭ ላሉ የሽግግር ፍትህ ስልቶች ትኩረት እንዳይሰጥ ወይም ስልቶቹ እውነትን እና እርቅን ማስፈን እንዳይችሉ ያደርጋል፡*
- *ሊከሰሱ የሚችሉ ሰዎች ከሙብዛታቸው የተነሳ የሽግግር ሂደቱ የክስ ሂደት ሊሸከም ከሚችለው በላይ እንዳይሆን ያሰጋል፡*
- *በግጭት እና በጭቀና የተሳተፈ እያንዳንዱን ግለሰብ ለህግ ማቅረብ ከተግባራዊነትም ሆነ በቴክኒክ ደረጃ የማይቻል፡ ከተሞከረም ፍትሃዊ እና ፍትሃዊ ያልሆኑ ቅጣቶችን የሚያስከትሉ የችኮላ ሂደቶችን የመከተል አዝማሚያ ስለሚኖረው የፍትህ መዛባት ሊያስከትል ይችላል።*

## 2.3. ተቋማዊ ጉዳዮች፡- የወንጀል ምርመራውን፣ ክስ የመመስረቱን እና የፍርድ ሂደትን ማን ያከናውነዋል?

### 2.3.1. ጠቅላላ

*በሽግግር ፍትህ ሂደት - የወንጀል ክስ በመመስረት ረገድ የሚነሳው ጥያቄ ይህንን ተግባር የሚያከናውኑት ተቋማት የትኞቹ መሆን አለባቸው የሚለው ነው። በተለይም በደሎቹ በተፈጸሙበት ወቅት የመብት ጥሰቶች ተሳታፊ የነበሩ ወይም አስቻይ ሁኔታ የፈጠሩ አካላት - ለምሳሌ የፖሊስ፣ የደህንነት፣ የአቃቤ ህግ እና የፍርድ ቤት ተቋማት እና አባላቶቻቸው - መሰረታዊ ለውጥ ሳያደርጉ ወይም ማድረጋቸው በህብረተሰቡ ዘንድ ሳይታመንበት - በሽግግር ፍትህ ሂደቱ መሳተፋቸው ተገቢ አይሆንም። በሀገራችንም ተመሳሳይ አውድ በመኖሩ በሽግግር ሂደቱ የክስ ሂደትን የሚመሩ ተቋማዊ አማራጮችን መመልከት ያስፈልጋል።*

Draft

### 2.3.2. ፍርድ ቤቶች

ፍርድ ቤቶችን በሚመለከት በአለምአቀፍ ደረጃ ያለው ተመክሮ የተለያየ መልክ ያለው ነው። በሰዎች መብቶች ላይ የሚፈጸሙ ከባድ አለምአቀፍ ወንጀሎችን በተመለከተ ያለው ልምድ፡ ሀ) አለምአቀፍ የወንጀል ፍርድ ቤት ወይም እንደየሀገራቱ ነባራዊ ሁኔታ በተለየ መልኩ የሚቋቋሙ አለምአቀፍ ፍርድ ቤቶችን በመጠቀም የዳኝነት ስርአቱን ማስኬድ (ለምሳሌ በዩጎዝላቪያ እና ሩዋንዳ እንደተደረገው) ወይም ለ) ሀገራዊ ፍርድ-ቤቶችን እና የአለምአቀፉን ስርአት በማዋሀድ ልዩ ፍርድ ቤቶችን በመመስረት የዳኝነት ስርአቱን ማስኬድ (ለምሳሌ በሴራሊዮን እና ካምቦድያ እንደተደረገው)፡ ወይም ሐ) አገራዊ የፍትህ ስርአቱን በመጠቀም የዳኝነት ስርአቱን ማስኬድ - የሚሉ ናቸው።

ኢትዮጵያ የአለምአቀፉ የወንጀል ፍርድ ቤት አባል ሀገር አይደለችም። በፍርድ ቤቱ የህግ ማዕቀፍ እና አሰራር መሰረት አባል ያልሆኑ ሀገራት ጉዳይ ለፍርድ ቤቱ ሊቀርብ የሚችልበት አካሄድ ቢኖርም - ከቅርብ ጊዜ ተመክሮዎች እና ከሽግግር ፍትህ ግቦች አንጻር የሚመከር አማራጭ አይደለም። ሌሎች የአለማቀፋዊ ፍርድ ቤት አማራጮችም (ለምሳሌ ቅይጥ ፍርድ ቤቶች) አሁን ካለው ተመክሮ አንፃር የሚበረታቱ ወይም በሀገራችን የፖለቲካ ሁኔታ ተቀባይነት የሚኖራቸው አይደሉም። ስለሆነም - ፍርድ ቤቶችን በሚመለከት - የሽግግር ፍትህ ሂደቱን ለማከናወን የሚከተሉት ሁለት አማራጮች ሊኖሩ ይችላሉ፡-

**አማራጭ አንድ፡- በከፍተኛ እና ጠቅላይ ፍርድ ቤት ውስጥ ልዩ ችሎት በማቋቋም ክሶቹን በመስማት ውሳኔ መስጠት፤**

ይህ አማራጭ አስፈላጊ የዳኞች ምደባ በማድረግ በፌደራል ፍርድ ቤት ውስጥ ለዚሁ ጉዳይ የሚሰየም ችሎት ነው። አማራጩ በከፍተኛ ፍርድ ቤት ውስጥ ያለፉ ጉልህ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶችን የሚያይ ልዩ ችሎት በማደራጀት እና ለሚመደቡት ዳኞችና ረዳቶቻቸው ተገቢ ስልጠና በመስጠት - ባለው የፍርድ ቤት መዋቅር ውስጥ ዳኝነቱን እንዲከናወን ያስችላል። የይግባኝ መብትን ለማስከበር ይግባኝ የሚሰማ ተመሳሳይ ልዩ ችሎች በጠቅላይ ፍርድ ቤት ውስጥ በማቋቋም ተግባራቱን እንዲያከናውን ይደረጋል።

***ጠንካራ ጎኖች***

- ተግባራቱ አሁን ባሉ ተቋማት ውስጥ እንዲከናወኑ ስለሚያደርግ ሀብት ይቆጥባል፡
- ያለውን የሰው እና የተቋም አቅም ለመጠቀም ያስችላል፡
- በፍርድ ቤቶች ገለልተኝነት እና አቅም ላይ ያለውን ጥያቄ ከመመለስ አንፃር - የተሻለ ነፃነት ያለው አወቃቀርና በተገቢ ማጣራት የታጀበ የዳኞች ምደባ በማሳለጥ በቀጣይ ፍርድ ቤቶቹ ለሚያደርጉት የለውጥ ስራ አስተዋፅኦ ይኖረዋል።

***ሥጋቶች***

- በቂ የሆነ ለውጥ ያልተደረገባቸው ወይም ተደርጎባቸዋል ተብለው የማይታሰቡ የፍርድ ቤት ችሎቶችን መጠቀም በክሶቹ ሂደት እና በውጤቶቹ ላይ የተአማኒነት እና የቅቡልነት ጥያቄ ያስነሳል፡
- አሁን ባለው ሁኔታ ከክሶቹ ውስብስብነት እና ግዝፈት አንፃር የአቅም ውስንነት ሊኖር ይችላል።

**አማራጭ ሁለት፡- ልዩ ፍርድ ቤት በማቋቋም ክሶቹን መስማት እና ውሳኔ መስጠት**

ይህ አካሄድ ከመደበኛ ፍርድ ቤቶች የተለየ የራሱ አደረጃጀት ያለው ልዩ ፍርድ ቤትን በህግ በማቋቋም፡ በጉዳዩ ላይ ልምድ ያላቸው ኢትዮጵያውያንን በዳኝነት በመሰየም፡ እና ለፍርድ ቤቱ ተገቢውን ስልጣን ሀላፊነት እና ነፃነት በመስጠት - የክስ ሂደቱን እንዲያስተዳድር የሚደረግበት አሰራር ነው።

***ጠንካራ ጎኖች***

- አዲስ ተቋም እና አደረጃጀት በመፍጠር የተሻለ ቅቡልነት እና ገለልተኝነት ያለው ተቋም እንዲኖር እድል ይፈጥራል፡
- የወንጀሎቹን ውስብስብነት የሚመጥን አቅም ያላቸውን ዳኞች ለመመደብ እና በተሻለ ብቃት ክሶቹን ለማስተናገድ ያስችላል።

*ሥጋቶች፡*

- ልዩ ችሎቶችን ከመሰየም አንፃር ህገ-መንግስታዊ ጥያቄዎች ሊነሱበት ይችላል፡
- አዲስ ተቋም ማቋቋም፡ እና የሰው ሀይል እና አስፈላጊ ግብአቶቹን የማሟላት ስራ ረጅም ጊዜ ይወስዳል፡
- አካሄዱ ዘላቂነት ላለው ተቋም ግንባታ ያለው አስተዋፅዎ አነስተኛ ነው።

### 2.3.3. ምርመራ እና ክስ

ምርመራና ክስን በሚመለከት የሚከተሉት ሁለት ተቋማዊ አማራጮች ሊኖሩ ይችላሉ።

**አማራጭ አንድ፡- በፖሊስ እና ዐቃቤ ህግ ተቋማት ውስጥ በሽግግር ፍትህ ሂደቱ የክስ ሂደት ምርመራ እና ክስ ላይ የሚሳተፉ የተለዩ ቡድኖችን ማዋቀር**

ይህ አማራጭ አሁን ያለውን መንግስታዊ መዋቅር በመጠቀም - የተሻለ ገለልተኝነት እና ነፃነት ለመስጠት እንዲቻል የተለዩ ቡድኖችን በማዋቀር የምርመራ እና የክስ ሂደቶችን ማስተባበርን ይጠይቃል። ይህ ማለት ተቋማቱ አሁን ባሉበት ሁኔታ እነዚህን ተግባራት ይተገብራሉ ማለት ሳይሆን - የተቋማዊ ማሻሻያ፡ የማጥራት እና የልየታ ተግባራትን በማከናወን ተግባሩን ይፈፅማሉ በሚል ቅድመ-ሁኔታ የሚቀመጥ ነው። በዚህ ሂደት ለሚሳተፉ አካላትም አለምአቀፍ ደረጃውን የጠበቀ ስልጠና መስጠት ያስፈልጋል።

*ጠንካራ ጎን*

- አሁን ባሉት ተቋማት ውስጥ ተግባራቱ እንዲከናወኑ ስለሚያደርግ ሀብት ይቆጥባል፡
- አሁን ያለውን የሰው እና የተቋም አቅም ለመጠቀም ያስችላል፡
- እንዲህ አይነት ስራዎችን የመስራት ልምድ ቀጣይነት እንዲኖረው በማድረግ ለተቋም ግንባታ አስተዋፅኦ ያደርጋል።

*ሥጋቶች*

- በቂ የለውጥ ስራ ባልተከናወነባቸው ወይም ተደርጎባቸዋል ተብለው የማይታሰቡ የፍትህ ተቋማትን በመጠቀም የክስ ስራዎችን ማካሄድ በሂደቱ እና በውጤቱ ላይ የተአማኒነት እና የቅቡልነት ጥያቄ ያስነሳል፡ ፡

**አማራጭ ሁለት፡- አሁን ካለው የዓቃቤ ሕግ ተቋማት ውጪ ሌላ የምርመራና ክስ ሂደቶችን የሚያስተባብር ልዩ የዓቃቤ ሕግ ተቋም በማቋቋም የፖሊስ እና የምርመራ ባለሙያዎችን መመደብ**

ይህ አማራጭ አሁን ካሉት የምርመራ እና ክስ ተቋማት ውጭ አዲስ እና ጊዜያዊ ልዩ የዓቃቤ ሕግ ተቋም በማቋቋም ተግባራቱን ለማከናወን ያስችላል። ይህ ተቋም የዓቃቤ ሕግን ብቻ ሳይሆን የምርመራ ስራ የሚሰሩ ባለሙያዎችንም በማካተት የሚቋቋም ይሆናል።

*ጠንካራ ጎን*



Draft

- አዲስ ተቋም እና አደረጃጀት በመፍጠር የተሻለ ቅቡልነት እና ገለልተኝነት ያለው ተቋም እንዲኖር እድል ይፈጥራል፡
- የምርመራ እና የክስ ስራው በአንድ ተቋም የሚሰራ በመሆኑ ስራውን በተሻለ ፍጥነት ለመስራት ያስችላል፡
- ለተቋሙ ልዩ ትኩረት ለመስጠት፣ አስፈላጊ ድጋፍ ለማግኘት ያስችላል፡
- የወንጀል ተጎጂዎችም ሆኑ ህብረተሰቡ ከተቋሙ ጋር በትብብር እንዲሰሩ ያበረታታል፡
- የተሻለ ባለቤትነት እና ተጠያቂነት ይፈጥራል።

***ሥጋቶች***

- አዲስ ተቋም የማቋቋም፣ የሰው ሀይል እና አስፈላጊ ግብአቶችን የማሟላት ስራ ረጅም ጊዜ ይወስዳል፡
- በምርመራም ሆነ በክስ ስራ አሁን ካሉት ተቋማት ውጪ ብቃት እና ልምድ ያላቸው ባለሙያዎችን ማግኘት አስቸጋሪ ሊሆን ይችላል፡
- ዘላቂነት ላለው ተቋም ግንባታ ያለው አስተዋፅኦ አነስተኛ ነው፡
- መንግስት ለዚህ ተቋም አስፈላጊ ነገሮችን የማሟላት ኃላፊነት ስለሚኖርበት በውስን የሀገር ሀብት ላይ ጫና ይፈጥራል።

### 2.3.4. የህግ ማሻሻያ ተግባራት፡- በሰብአዊነት ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎችን በሀገራችን ህግ ማካተት

በሰዎች ላይ ከሚፈጸሙ የጭካኔና አሰቃቂ አለም-አቀፍ ወንጀሎች ውስጥ አንዱ የሆነው በሰብአዊነት ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች - በሀገራችን የወንጀል ህግም ሆነ በሌሎች ህጎች አልተደነገገም። ይህም በሽግግር ፍትህ ሂደት ለሚከናወኑ የወንጀል ክሶች እንቅፋት ሊሆን የሚችል የህግ ክፍተት ነው። በመሆኑም በዓለምአቀፍ የወንጀል ሕግ መሰረት በሰብአዊነት ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎችን በሚመለከት ህግ በማውጣት ያለውን ጉድለት መሙላት አስፈላጊ ይሆናል። ይህም በምርመራም ሆነ በፍርድ ሂደት ገዢ የህግ ድንጋጌ እንዲኖር በማድረግ - በጉልህ ሰብአዊ መብት ጥሰቶች ላይ የሚደረገውን የክስ ሂደት ወጥ እና ፍትሃዊ ለማድረግ ይረዳል።

ይህ አካሄድ የወንጀል ህግ ወደኋላ ተመልሶ የማይሰራ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ - ማንኛውም ተግባር ወይም ድርጊት በተፈጸመ ጊዜ በወንጀል የሚያስጠይቅ ስለመሆኑ በግልጽ የተደነገገ ካልሆነ በቀር ማንኛውንም ሰው አያስጠይቅም የሚል ክርክር ማስነሳቱ የሚጠበቅ ነው። ይሁንና እነዚህ ወንጀሎች ቀድሞውንም ቢሆን በአለም-አቀፉ የልማድ ህግ (customary international law) መሰረት ወንጀል ስለመሆናቸውን ሀገራት በጋራ የተስማሙበት አለምአቀፍ መርህ ነው። ከዚህ አንፃር - ሀገራት እውቅና በሰጡት አጠቃላይ የህግ መርህ መሰረት ድርጊቱ እንደ ጥፋት የሚቆጠር ከሆነ - የወንጀል ህግ ወደ ኋላ ተመልሶ አይሰራም የሚለው መርህ ተፈጻሚ አይሆንም በማለት የሲቪል እና ፖለቲካ መብቶች አለም አቀፍ ቃልኪዳን ስምምነት በአንቀጽ 15(2) ላይ በግልጽ የሚደነገግ መሆኑን ማየት ያስፈልጋል። ስለሆነም በህገ-መንግስቱ አንቀጽ 13(2) መሰረት መሰረታዊ መብቶችና የነጻነት ድንጋጌዎች ኢትዮጵያ ከተቀበለቻቸው አለም-አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ህግጋት፣ ስምምነቶችና መርሆች ጋር ተጣጥመው የሚተረጎሙ በመሆኑ - ወደፊት የሚወጣውን ህግ መሰረት በማድረግ - ከህጉ መውጣት በፊት በሰብአዊነት ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎችን በከወኑ ግለሰቦች ላይ ክስ በማቅረብ ተጠያቂ ማድረግ ይቻላል፡ ተገቢም ነው። ስለሆነም እንዲህ አይነት ህጎች ሲወጡ - ለፍርድ ሂደቱ እንዲያመች በአለማቀፍ ሕግ የተደነገገን ወንጀል እውቅና የመስጠት ውጤት ይኖራቸዋል እንጂ አዲስ ህግ እንደማውጣት ሊቆጠር አይገባም።



Draft

## 2.4. እውነትን ማፈላለግ እና ይፋ ማውጣት

### 2.4.1. ጠቅላላ

በሽግግር ፍትህ ሂደት እውነት ማፈላለግ ያለፈን የሰብአዊ መብት ረገጣ እና የደረሰን ጉዳት የማወቅ እና በይፋ እውቅና የመስጠት ሂደት ነው። ተጎጂዎች ወይም ቤተሰቦቻቸው እና ማህበረሰቡ በአጠቃላይ ያለፈውን እውነት የማወቅ መብት አላቸው። እውነትን ማፈላለግ እና ይፋ ማውጣት በራሱ ለተበዳዮች እና ለተበዳይ ቤተሰቦች የፍትህ አይነት ነው። በሀገር ደረጃም የነበሩት ክስተቶች በይፋ እውቅና ሲሰጣቸው በይፋ ተገልፀው የሀገሪቱ ታሪክ አካል ሲሆኑ ለትውልድ እና ለብሔራዊ እርቅ መሰረት ይጥላሉ። በሀገራችን የሚታሰበው የሽግግር ፍትህ ሂደትም እነዚህን አላማዎች የሚያሳካ መሆን ይጠበቅበታል።

### 2.4.2. እውነትን በማጣራት ሂደት ዋና ዋና ተግባራት ምንድን ናቸው?

**የተጎጂዎችን ተሳትፎ ማረጋገጥ፡-**

እውነትን በማጣራት ሂደት ውስጥ የተጎጂዎችን ተሳትፎ ማረጋገጥ መሰረታዊ ጉዳይ ነው። ጉዳት ለደረሰባቸው ሰዎች - የደረሰባቸውን ጉዳት በዝርዝር እንዲያስረዱ በማድረግ እውነቱን በማጥራቱ ሂደት ተሳትፎ እንዲኖራቸው ማድረግ ያስፈልጋል።

**ጥፋት ፈፃሚዎችን ማሳተፍ፡-**

በእውነት ማውጣት ሂደት የተበዳዮች ያለፈ ሁኔታ ትውስት - በተበዳዮች የተወሰኑ ክስተቶች ላይ የተገደበ እንዳይሆን እና የቀረ ምስክር/ተጎጂ የሌለባቸው ጥሰቶች ደግሞ ሳይጣሩ እንዳይቀሩ የበዳዮችን ተሳትፎ ማረጋገጥ ያስፈልጋል። የተበዳዮች ምስክርነት ስራ ከምንም በላይ አስፈላጊ መሆኑ የማያጠራጥር ቢሆንም - ስለእውነቱ የበለጠ እውነትን ለማግኘትና የነበረውን አጠቃላይ ስእል ለመመስረት - በተለይም በዳዮች የወንጀሉ እቅድ፡ መሪ፡ አላማ፡ ስርአት ወዘተ እንዴት እንደነበር ለማስረዳት የሚችሉበት፡ የተሰወሩ ወይም ያሉበት/የተቀበሩበት ቦታ የማይታወቁ ሰዎች ቤተሰቦችም ስለሁኔታው የሚያውቁበት እና የሚረዱበትን እድል ይፈጥራል።

**በደሎችን መሰነድ፡-**

ያለፉ ከፍተኛ የሰብአዊ መብት ጥሰቶችን ዝርዝር መረጃ መሰነድ ጥፋቶች እንዲታወቁና እንዳይደገሙ ያደርጋል። በተጨማሪም - በሽግግር ፍትህ ሂደቱ ታሪካዊ እውነታው ተረጋግጦና ተሰንዶ በመቀመጡ ለተበዳዮች ዕውቅና በመስጠት ወደፊት ከሚኖር 'ይህ አልተፈፀመም' አገላለጽ ወይም ክህደት ተጎጂዎችን የሚጠብቁ ይሆናል።

**የተጣራውን እውነት ለማህበረሰቡ ማሳወቅ እና ይፋ ማውጣት፡-**

እውነትን በማጣራት ሂደት በደሎችን መሰነድ ብቻውን በቂ አይደለም። ስለሆነም የተጣራውን እውነት ለማህበረሰቡ ማሳወቅ እና ለተጎጂዎች ሰቀቃ ሕዝባዊ እውቅና መስጠት ያስፈልጋል።

### 2.4.3. ተቋማዊ ጉዳዮች፡- እውነትን የማጣራት ሂደት ማን ያከናውነዋል?

በሽግግር ፍትህ ሂደት እውነትን የማጣራት ተግባር በዋናነት የተጎጂዎች እና ጥፋት ፈፃሚዎችን ቃል የመሰብሰብ (statement taking) እና ህዝባዊ መድረኮችን (public hearing) የማመቻቸት ስራ ያካትታል። በሀገራችን በሚታሰበው የሽግግር ፍትህ ሂደት ይህንን ተግባር ለማከናወን የሚከተሉት ተቋማዊ አማራጮች ሊታዩ ይችላሉ።

**አማራጭ አንድ፡- ስራውን አዲስ በሚቋቋም ኮሚሽን አማካኝነት ማከናወን**

በሌሎች ሀገራት ልምድ በብዛት እንደታየው - በሽግግር ፍትህ ሂደት እውነትን የማጣራት ተግባር በሂደቱ ለሚቋቋሙ የእውነት አጣሪ ኮሚሽኖች የሚሰጥ ስራ ነው። በኢትዮጵያም አንደኛው አማራጭ ይህንን ተግባር ነጻና ገለልተኛ ሆኖ ለሚቋቋም የእውነት እና የእርቅ ኮሚሽን መስጠት ነው።

Draft

**ጠንካራ ጎኖች**

- በሽግግር ፍትህ ሂደት ኮሚሽን ማቋቋም አለምአቀፍ ተቀባይነት ያለው እና የተለመደ አካሄድ ነው፡
- አዲስ ተቋም እና አደረጃጀት በመፍጠር የተሻለ ቅቡልነት እና ገልልተኝነት እንዲኖር እድል ይፈጥራል፡
- የእውነት ማጣራቱ አላማ እውነቱን በማጣራትና ምህረት በመስጠት እርቅን ማስፈን እንደመሆኑ ይህ ሂደት ተግባሩን ለመፈጸም በተቋቋመ አካል መሰጠቱ ይበልጥ ውጤታማ ያደርገዋል፡
- እነዚህ ተቋማት ካላቸው ነጻነት፣ ገለልተኛነት እና በሂደታቸውም ማህበረሰቡን የሚያሳተፉ በመሆኑ የሂደቱ ተአማኒነት ከፍ ያለ ይሆናል፡
- በዘርፉ ታዋቂ የሆኑ ባለሙያዎች እና አመራሮችን የተቋሙ አካል በማድረግ ስራው በእውቀት እንዲመራ ያስችላል፡
- እውነት በቅድመ-ሁኔታ ላይ ለሚሰጥ ምህረት ቅድመ-ሁኔታ እንደመሆኑ መጠን - የበዳዮችን እና ተጎጂዎችን ተሰሚነት እና ተሳትፎ ማረጋገጥ፣ ማጣራት፣ መሰነድ እና ይፋ የማድረግ ሂደቶችን የሚያሳልጡ መጠነ-ሰፊ ስራዎች/መድረኮች/የቃል መቀበያ መንገዶች መዘርጋትን ይጠያቃል፡ ይህ አይነቱን ሰፊ ስራ ይህን በተግባር ለመፈጸም አላማ ሲባል በተቋቋመ ኮሚሽን መከናወኑ ይበልጥ ተገቢ ነው።

**ስጋቶች**

- በሀገር ካለው ውስን ሀብት አንፃር ከፍተኛ ወጪን የሚጠይቅ ነው፡
- አዲስ ኮሚሽን ማቋቋም ከዚህ ቀደም ተሞክሮ የነበረ በመሆኑ የፖለቲካ ተነሳሽነቱ ዝቅተኛ ሊሆን ይችላል፡
- ከሀገሪቱ የቆዳ ስፋት፣ ከሂደቱ ስፋት አንፃር እና ኮሚሽኑ ከሚኖረው የጊዜ ገደብ አንፃር የተደራሽነት ችግር ሊኖር ይችላል።

**አማራጭ ሁለት፡- በኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን ወይም በቅርቡ በተቋቋመው የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን አማካኝነት እውነት የማጣራቱን ተግባር ማከናወን**

ይህ አማራጭ ተገቢ የህግ ማሻሻያ በማድረግ እና ተጨማሪ ስልጣን በመስጠት - እነዚህ ተቋማት በሽግግር ፍትህ ሂደቱ እውነት የማጣራት ተግባር እንዲያከናውኑ ማድረግን ይተልማል።

**ጠንካራ ጎኖች**

- አሁን ባሉት ተቋማት በመጠቀም የሀገርን ውስን ሀብት ይቆጥባል፡
- ተቋማዊ አቅምን ይገነባል።

**ስጋቶች**

- ሁለቱም ተቋማት ከፍተኛ ሀላፊነት እና መጠነ ሰፊ ተግባራት ያሏቸው በመሆኑ እውነትን የማጣራት ሰፊ ስራን በውጤታማነት ላያከናውኑት ይችላሉ፡
- በተለይም የሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን ብሄራዊ የሰብአዊ መብት ተቋም ከመሆኑ አንፃር - በቁጥጥር እና ክትትል ተግባራቱ ላይ ተጽእኖ ያሳድርበታል፡ በአለምአቀፍ ተመክሮም እንዲህ አይነት ተቋማት በሂደቱ ቀጥተኛ ፈፃሚ እንዲሆኑ አይመከርም፡

Draft

- በሽግግር ፍትህ ሂደቱ እውነትን ለማጣራት መከናወን የሚያስፈልገውን ውስብስብ ተግባር እና አሳታፊ ሂደት ተከትሎ ለመስራት የሚያስችል አቅም የላቸውም፣
- ከተቋማቱ ውጪ ያሉ በዘርፉ እውቀት ያላቸውን ባለሙያዎች እና አመራሮችን በሂደቱ ለመጠቀም እድል አይሰጥም።

## 2.5. እርቅ

### 2.5.1. ጠቅላላ

እርቅ የሽግግር ፍትህ ሂደት አንደኛው ግብ ወይም አላማ ነው። እርቅ በነበረ መጠነ-ሰፊ የሰብአዊ መብት ጥሰት፣ ጦርነት፣ ግጭት፣ ወይም ጭቆና ባስከተለው መጎዳዳት፣ ጥላቻና መፈራራት ምክንያት ተለያይተው፣ ተራርቀው እና ተቀራርጠው የነበሩ ሰዎችንና የህብረተሰቦች ክፍሎች - የፈረሰው የጋራ ኑሯቸው እና ግንኙነታቸውን እንደገና ለመገንባት የሚጓዙበት ሂደት ነው።

በሽግግር ፍትህ ሂደት እርቅ የሚኖረው ሚና በሽግግሩ ባህሪ ላይ የሚመሰረት ሲሆን - በተለይም እንደ ኢትዮጵያ ባሉ አገራት - የሰብአዊ መብት ጥሰቶች ሲፈፀሙባቸው በነበሩ ስርአቶች ውስጥ ተሳታፊ የነበሩ አመራሮች ወይም ግለሰቦች - ለእርቅ ከፍተኛ ሚና እንዲጫወቱ ማድረግ ያስፈልጋል።

በሽግግር ፍትህ አውድ እርቅ አንድ ሂደት ወይም በራሱ ግብ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል። እርቅ እንደ ሂደት የሚታይበት ሁኔታ - ጥልቅ፣ ረጅም፣ ቀጥተኛ ያልሆነ እና ተለዋዋጭ ሂደትን የሚያካትት ሲሆን - ዘርፈ-ብዙ ስልቶችን በመተግበር ሰላም፣ መግባባት እና ፍትህን ለማስፈን እንደሚያግዝ ሂደት ተደርጎ ይወሰዳል። እርቅ ግብ ተደርጎ በሚወሰድበት ሁኔታ ደግሞ - የተለያዩ ስልቶችን በመተግበር የሚሳካ ወይም ሊሰፍን የሚችል ግብ ይሆናል። በአጭሩ እርቅ እንደ ግብ ሲወሰድ የተለያዩ የሽግግር አላባዎችን ስራ ላይ በማዋል ማስፈን ይቻላል የሚል ሀሳብን ያዘለ ሲሆን፣ እርቅ እንደ ሂደት የሚወሰድበት አረዳድ ደግሞ - በተወሰነ ጊዜ ብቻ ሊሰፍን የሚችል ግብ ሳይሆን ረጅም ጊዜ የሚፈጅ ስራ ስለሆነ - ከዚህ አንጻር የሽግግር ስልቱ አላማ - የእርቅ ጉዞውን ማስጀመር እና ማመቻቸት ሊሆን ይገባል የሚል ነዉ።

እርቅ ከሌሎች የሽግግር ፍትህ ሂደት መንገዶች ጋር ተቀናጅቶ የሚከናወን እንጂ ያለምንም ተጠያቂነት የኋላ በደልን ይቅር የማለት ሂደት መሆን የለበትም። ስለሆነም ሂደቱ - ከበደል ፈፃሚዎች እውቅና እና ጸጸት፣ ከተጎጂዎች ይቅርታ መስጠት፣ ተበቃይ ያልሆነ አብሮ መኖር፣ ከዴሞክራሲያዊ ውሳኔ እና ዳግም ውህደት፣ እንዲሁም እውነትን፣ ምሕረትን፣ ማካካሻን፣ ሰላምን እና ፍትህ በአንድነት የያዘ ስራ አንድ ክፍል መሆን አለበት።

### 2.5.2. በሽግግር ፍትህ ሂደት ሊከናወኑ የሚችሉ የእርቅ አይነቶች

በሚታሰበው የሽግግር ፍትህ ሂደት የሚከተሉትን የእርቅ አይነቶች በተለያየ መጠን እና ደረጃ መተግበር ያስፈልጋል፡ ፡

**ግላዊ እርቅ፡-**

ጉዳት ፈፃሚዎች ከሌሎች ጋር ያላቸውን ግንኙነት እንዲያድሱ ለማድረግ ከራሳቸው ጋር ሰላም እንዲፈጥሩ ማድረግን ታሳቢ ያደረገ ነው። ከጉዳት የማገገሚያ ፕሮግራሞችን በመቅረፅ ለተጎጂዎች ቁሳዊ እና ስነልቦናዊ ድጋፎች የሚደረግበትን መንገድ ማመቻቸትን ይጠይቃል።

**የግለሰቦች እርቅ፡-**

በበዳዮች እና በተበዳዮች እንዲሁም በጉዳቱ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መልኩ ተሳታፊ በነበሩ ሰዎች መካከል ባለው ግንኙነት ላይ በማተኮር - ለደረሰው በደል እውቅና የመስጠት፣ የመለወጥ እና ይቅር የመባባል ሂደት ነው። በሽግግር

Draft

ፍትህ ሂደት በክስ፡ በእውነት ማጥራት እና በምህረት ሂደቶች ጭምር - በሀይማኖታዊ እና ማህበረሰባዊ እሴቶች ላይ ትኩረት በማድረግ - የሚከናወኑ የእርቅ ሂደቶችን ይጨምራል።

**ማህበራዊ እና ፖለቲካዊ እርቅ፡-**

በተከፋፈሉ እና ቅራኔ ውስጥ በገቡ የብሄር፡ የማህበረሰብ፡ የሀይማኖት፡ የፖለቲካ ወይም ሌሎች ቡድኖች ላይ ትኩረት በማድረግ - ባህላዊ እና ሀይማኖታዊ የእርቅ እና ግጭት አፈታት መንገዶችን በመጠቀም - ለደረሰው ጉዳት እውቅና የመስጠት እና በመከባበር ላይ የተመሰረተ ግንኙነት ወደፊት ለመመስረት የሚከናወን የእርቅ አይነት ነው።

**ተቋማዊ እርቅ፡-**

የሰዎችን ሰብአዊ መብቶች ለመጠበቅ፡ ለማስጠበቅ እና ለማሟላት ሀላፊነት የነበረባቸው ተቋማት - በተለይም በሽግግር ፍትህ ሂደቱ ወቅት ወሳኝ ሚና የሚጫወቱ የፍትህ እና የፀጥታ ተቋማት - ተቋማዊ ማሻሻያ በማድረግ እና ተጠያቂነት በመመስረት የደረሰውን ጉዳት አምነውና ሀላፊነት ወስደው የህብረተሰቡን እምነት መልሰው የሚያገኙበትን መንገድ የማመቻቸት ሂደት ነው።

### 2.5.3. ተቋማዊ ጉዳዮች፡- የእርቅ ሂደትን ማን ያከናውነው?

በሽግግር ፍትህ ሂደት ውስጥ የእርቅ ሂደት ከክስ፡ ከእውነት ማጣራት እና ከምህረት ሂደቶች ጋር ተሳስሮ የሚከናወን ተግባር ነው። በሀገራችን በሚታሰበው የሽግግር ፍትህ ሂደት ይህንን ተግባር ለማከናወን የሚከተሉት ተቋማዊ አማራጮች ሊታዩ ይችላሉ።

**አማራጭ አንድ፡- አዲስ በሚቋቋም ኮሚሽን አማካኝነት ማከናወን**

ከሌሎች ሀገሮች ልምድ እንደታየው - በሽግግር ፍትህ ሂደት የእርቅ ተግባር በሂደቱ ለሚቋቋሙ ኮሚሽኖች የሚሰጥ ስራ ነው። በኢትዮጵያም አንደኛው አማራጭ ይህንን ተግባር ነጻና ገለልተኛ ሆኖ በሚቋቋም የእውነት እና የእርቅ ኮሚሽን እንዲከናወን ማድረግ  ነው።

**ጠንካራ ጎኖች**

- በሽግግር ፍትህ ሂደት እርቅ አንደኛው ግብ እንደመሆኑ በዚህ ሂደት ተግባራቱን ለመፈጸም በተቋቋመ አካል መከናወኑ ይበልጥ ውጤታማ ያደርገዋል፡
- እነዚህ ተቋማት ካላቸው ነጻነትና ገለልተኛነት እና በሂደቱም ማህበረሰቡን የሚያሳትፉ በመሆኑ ተአማኒነቱ/ ቅቡልነቱ ከፍ ያለ ይሆናል፡
- በዘርፉ ታዋቂ ባለሙያዎች እና አመራሮችን የተቋሙ አካል በማድረግ ስራው በእውቀት እንዲመራ ያስችላል፡ ፡

**ስጋቶች**

- በሀገር ካለው ውስን ሀብት አንፃር ከፍተኛ ወጪ የሚጠይቅ ነው፡
- አዲስ ኮሚሽን ማቋቋም ከዚህ ቀደም ተሞክሮ የነበረ በመሆኑ የፖለቲካ ተነሳሽነቱ ዝቅተኛ ሊሆን ይችላል፡
- ከሀገሪቱ የቆዳ ስፋት፡ ከሂደቱ ጥልቀት አንፃር እና ኮሚሽኑ ከሚኖረው የጊዜ ገደብ አንፃር የተደራሽነት ችግር ሊኖር ይችላል።

**አማራጭ ሁለት፡- የእርቅ ተግባራቱን በኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን ወይም በኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን አማካኝነት ማከናወን፡**

Draft

ይህ አማራጭ ተገቢ የህግ ማሻሻያ በማድረግ እና ተጨማሪ ስልጣን በመስጠት - በሽግግር ፍትህ ሂደቱ የእርቅ ተግባራትን የማከናወን ተግባር ለሀገራዊ ምክክር ኮሚሽኑ ወይም ለሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን እንዲሰጥ ማድረግን የሚመለከት ነው።

**ጠንካራ ጎኖች**

- አሁን ባሉት ተቋማት በመጠቀም በሀገር ያለውን ውስን ሀብት ይቆጥባል፣
- የሚነሱበት ትችቶች እንደተጠበቁ ሆኖ ከገለልተኝነት እና ነፃነት አንፃር የተሻለ ተቀባይነት ሊኖረው ይችላል፡

**ስጋቶች**

- ኮሚሽኑ ከፍተኛ ሀላፊነት እና መጠነ-ሰፊ ተግባራት የተሰጠው በመሆኑ የእርቅ ተግባራትን በውጤታማነት ለማከናወን ይቸገራል፡
- አሁን ያለው የኮሚሽኑ ስልጣን ይህን የማያካተት በመሆኑ የህግ ማሻሻያ ያስፈልጋል፡ ይህም ጊዜ ይወስዳል፡
- አሰራሩም ከምክክር ኮሚሽኖች ለየት ያለ ስልጣን የሚሰጠው በመሆኑ ከአለማቀፍ ልምድ ጋር ያለመጣጣም ችግር ሊኖር ይችላል፡
- በሽግግር ፍትህ ሂደቱ እርቅን ከሌሎች ሂደቶች ጋር አቀናጅቶ በመተግበር ረገድ ክፍተት ሊፈጠር ይችላል፡

## 2.6. ምህረት

### 2.6.1. ጠቅላላ

በሽግግር ፍትህ ሂደት ምህረት እንደ አንድ የመሸጋገሪያ መፍትሄ ይወሰዳል። ምህረት ለሰላም ግንባታ፡ ተጨማሪ ግጭቶችን ለመከላከል፡ እና ማህበረሰቦችን ለማከም ከፍተኛ ፋይዳ አለው። ይሁንና በአሁኑ ጊዜ ሰፊ ተቀባይነት ያገኘው እሳቤ - ያለቅድመ-ሁኔታ የሚሰጥ ምህረት የፍትህ መጓደልን ስለሚያስከትል እና ተጠያቂነት እንዳይኖር በማድረግ ለቀጣይ ቁርሾ መነሻ ስለሚሆን ተቀባይነት አይኖረውም የሚል ነው። አለምአቀፍ እና አህጉራዊ የሰብአዊ መብት ድንጋጌዎችም - ጉልህ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶችን ለፈፀሙ ሰዎች ያለቅድመ ሁኔታ የሚሰጥ ምህረት - ሰብዓዊ መብቶችን የማረጋገጥ ግዴታን የሚጣረስ መሆኑን ያስቀምጣሉ።

በኢትዮጵያ ለመተግበር በሚታሰበው የሽግግር ፍትህ ሂደት - በተለያየ ደረጃ ጥፋት ለፈፀሙ ሰዎች ቅድመ ሁኔታዎችን ባሟላ መልኩ ምህረት የሚደረግበትን መንገድ መዘርጋት አስፈላጊ ይሆናል። ምህረት ለመስጠት የሚያስችሉ ቅደመ-ሁኔታዎችን በግልጽ ማስቀመጥ፡ ምህረት የሚሰጥባቸውን የወንጀል አይነቶች መወሰን፡ የምህረት አሰጣጥ ስነ-ስርአትና ሂደቶችን መዘርዘር፡ እንዲሁም ምህረት የመስጠትን ሂደት ግልጽና ገለልተኛ በሆነ መንገድ የሚያስተናግዱ ተቋማት እና አደራጃጀቶችን መወሰን ያስፈልጋል።

### 2.6.2. የምህረት ሂደቱ ቅድመ-ሁኔታዎች ምን ሊሆኑ ይችላሉ?

ከአለማቀፉ ተመክሮ ለመረዳት እንደሚቻለው ምህረት ለመስጠት የሚከተሉት እንደ ቅድመ-ሁኔታ ሊቀመጡ ይችላሉ፡

**የአጥፊዎች ተሳትፎ መጠን፡ የወንጀል ይዘት እና ክብደት፡-**

በሽግግር ፍትህ ሂደት ምህረት ለማግኘት ግለሰቡ በወንጀሉ ያለው የተሳትፎ መጠን ግንዛቤ ውስጥ መግባት ይኖርበታል። ምህረት ከባድ በሆኑ ወንጀሎች ተጠያቂ የሆኑ ሰዎች ከተጠያቂነት ለማምለጥ የሚጠቀሙበት መሳሪያ መሆን የለበትም።

**የአጥፊዎችን ተሳትፎ ማረጋገጥ፡-**

የሽግግር ፍትህ ሂደት ጥፋት ፈፃሚዎች በሂደቱ እንዲሳተፉና ትብብር እንዲያደርጉ የሚጠይቅ እንደመሆኑ መጠን - በምህረት የህግ ጥበቃ ማግኘታቸው - በሂደቱ ተሳታፊ ለመሆን እንዲበረታቱ ያደርጋል። ስለሆነም በክስ፣ በእርቅ፣ በካሳ እና እውነትን በማፈላለግ ሂደት ተሳትፎ ማድረጋቸው እንደ ቅድመ-ሁኔታ ሊቀመጥ ይችላል።

**እውነትን ማውጣት፡-**

ከሽግግር ፍትህ ምሰሶዎች አንዱ እውነት እንደመሆኑ መጠን - በቅደመ-ሁኔታ የሚሰጥ ምህረት እውነትን ለማጥራት ሁነኛ ሚና ይጫወታል። በዳዮች የወንጀሉን እቅድ፣ መሪ፣ አላማ፣ እና አጠቃላይ ሁኔታ ምን መልክ እንደነበረው ለሚመለከተው አካል ቀርበው እውነቱን መንገር እና ያደረሱትን በደል በመዘርዘር፣ በመጸጸትና ይቅርታ በመጠየቅ - የእውነትና የእርቅ ሂደቱን ማገዝ ይጠበቅባቸዋል።

**መፀፀት እና ይቅርታ መጠየቅ፡-**

በሽግግር ውስጥ ያለ ማህበረሰብ እና በደል የደረሰባቸው ሰዎች ለተፈፀመባቸው በደል ፍትህ ከማግኘት ባለፈ - ያለፈው እንዳይደገም መተማመኛ ይፈልግሉ። ጥፋት አድራሾች ስለጥፋታቸው መጸጸታቸውን እንዲገልጹ እና ይቅርታ እንዲጠይቁ ማድረግ ያስፈልጋል።

**መተባበር፡-**

በዳዮች እንደ አስፈላጊነቱ እና አግባብነቱ - ከሌሎች የፍትህ አካላት ጋር መተባበር፣ በመልሶ ማቋቋም ፕሮግራሞች መሳተፍ፣ በባህላዊ የፍትህ ሂደቶች ውስጥ መሳተፍና መተባበር፣ በህገ-ወጥ መንገድ የተገኙ ንብረቶችን አሳልፎ መስጠት፣ በቁሳቁስ እና/ወይም በምሳሌያዊ ሁኔታ ለማካካሻ ስራ አስተዋፅኦ ማድረግ፣ እና የመሳሳሉ ተግባራትን ማከናወናቸውን ማረጋገጥ ያስፈልጋል።

### 2.6.3. ተቋማዊ ጉዳዮች፡- ምህረት የመስጠት ሂደትን ማን ያከናውነዋል?

በሽግግር ፍትህ የምህረት ሂደቱ አቀራረጽና ይዘት መሰረታዊ የመሆኑን ያህል - ምህረት የሚሰጠው አካል ህጋዊነት እና ቅቡልነትም ለስኬቱ ትልቅ ሚና ይጫወታል። በዚህ ረገድ የሚከተሉትን አማራጮች መመልከት ይቻላል።

**አማራጭ አንድ፡ አዲስ ኮሚሽን በማቋቋም ምህረትን በኮሚሽኑ አማካኝነት መስጠት፣**

በሌሎች ሀገሮች ልምድ እንደታየው - በሽግግር ፍትህ ሂደት ፍትህ - ከእውነት ማግኘት ጋር ተዛምዶ የሚሰጥ ምህረት ግቡን እንዲያሳካ እና ተግባራዊ አፈጻጸሙም ስኬት እንዲያገኝ ለማድረግ - የምህረት ሂደቱን ነጻና ገለልተኛ ሆኖ በሚቋቋም የእውነት እና የእርቅ ኮሚሽን አማካኝነት መምራት ይቻላል። የምህረቱን አካሄድ በተመለከተ - የሽግግር ፍትህ ሂደቱን በሚገዛው የህግ ማእቀፍ ውስጥ አስፈላጊ የህግ ድንጋጌዎች እንዲኖሩ ማድረግ ያስፈልጋል።

**ጠንካራ ጎኖች**

- የምህረቱ አላማ እውነትን ማውጣትና እርቅን ማስፈን እንደመሆኑ መጠን በዚህ ሂደት ተግባሮቹን ለመፈጸም በተቋቋመ ልዩ አካል መሰጠቱ ይበልጥ ውጤታማ ያደርገዋል፣
- በዘርፉ ታዋቂ የሆኑ ባለሙያዎች እና አመራሮችን የተቋሙ አካል በማድረግ ስራው በእውቀት እንዲመራ ለማድረግ ያስችላል፣
- ተቋማቱ ካላቸው ነጻነትና ገለልተኛነት እና በሂደታቸውም ማህበረሰቡን የሚያሳትፉ ከመሆኑ አንፃር ማህበረሰቡ ያመነበት እና ወደ ዘላቂ ሰላም የሚሸጋገር ምህረት እንዲሰጥ ያስችላል፣
- አጥፊዎችን እምነት ኖሯቸው በሂደቱ እንዲሳተፉ በማድረግ የሽግግር ስርአቱን ቀልጣፋ ያደርገዋል፣



Draft

- በስራ ሂደት ፍሰት ደረጃ ምህረት ቅድመ-ሁኔታዎች መሟላታቸውን፡ ሰዎች ለምህረት ብቁ መሆናቸው ማረጋገጥን፡ የተጎጂዎችን ተሰሚነት እና ተሳትፎ ማረጋገጥን፡ ምህረት ከተሰጠ በኋላ የሚኖሩ መመዘኛዎች መሟላታቸውን ማጣራትን፡ እንዲሁም የምህረቱ ቀጣይነትን ለማረጋገጥ የሚሰሩ በርካታ ስራዎችን የሚጨምር እንደመሆኑ መጠን - ይህ ተግባር ለዚሁ አላማ በተቋቋመ ኮሚሽን መሰጠቱ አግባብነት ይኖረዋል።

**ስጋቶች**

- ይህ አማራጭ በሀገር ካለው ውስን ሀብት አንፃር ከፍተኛ ወጪ የሚጠይቅ ነው፡
- አዲስ ኮሚሽን ማቋቋም ከዚህ ቀደም ተሞክሮ የነበረ በመሆኑ የፖለቲካ ተነሳሽነቱ ዝቅተኛ ሊሆን ይችላል፡
- ከሀገሪቱ የቆዳ ስፋት፡ ከሂደቱ ጥልቀት እና ኮሚሽኑ ከሚኖረው የጊዜ ገደብ አንፃር የተደራሽነት ችግር ሊኖር ይችላል፡

**አማራጭ ሁለት፡ አሁን ያለውን የምህረት አሰጣጥ አደረጃጀት በማሻሻል ለሽግግር ፍትህ ሂደቱ በመጠቀም ምህረትን መስጠት፡**

ይህ አካሄድ የምህረት አሰጣጥና አፈጻጸም ስነስርአት አዋጅ ቁጥር 1089/2010ን በማሻሻል እና ለሽግግር ጊዜ ፍትህ ተገቢ በሆነ መልኩ በመቃኘት - የፍትህ ሚኒስቴር፡ የምህረት ቦርዱ፡ እና ጠቅላይ ሚኒስትሩ ምርመራ እና ውሳኔ የሚሰጡበትን ሂደት መከተል ማለት ነው።

**ጠንካራ ጎኖች**

- አሁን ያሉ ተቋማትን በመጠቀም በሀገር ያለውን ውስን ሀብት ይቆጥባል፡
- ተቋማዊ አሰራርን ያዳብራል፡ አቅምን ይገነባል፡

**ስጋቶች**

- አሰራሩ በሽግግር ፍትህ መንፈስ የተቀረፀ ባለመሆኑ መሰረታዊ ማሻሻያዎች ያስፈልጉታል፡
- በሽግግር ፍትህ ሂደቱ ምህረት አሰጣጥ የሚኖረውን ውስብስብ ተግባራት እና መከተል ያለበትን አሳታፊ ሂደት ተከትሎ ለመስራት የሚያስችል አደረጃጀት አይኖረውም፡
- ተአማኒነቱ እና ቅቡልነቱ ጥያቄ ውስጥ የሚገባ ነው፡
- አጥፊዎች እምነት ኖሯቸው በሂደቱ እንዲሳተፉ ለማድረግ አያስችልም፡

### 2.6.4. ምህረት በህግ አግባብ የሚሰጥበት ሁኔታ

በኢፌዲሪ ህገ-መንግስት አንቀጽ 28 መሰረት - ኢትዮጵያ ባጸደቀቻቸው አለምአቀፍ ስምምነቶች እና በሌሎች የኢትዮጵያ ህጎች በሰው ልጅ ላይ የተፈጸሙ ወንጀሎች ተብለው የተወሰኑትን የወንጀል ድርጊቶች[4] - በማንኛውም የመንግስት አካል በይቅርታ ወይም በምህረት የማይታለፉ መሆኑ ተደንግጓል። ይህ አቀራረጽ በሽግግር ፍትህ ሂደት ምህረት ሊጠየቅባቸው የሚችሉ አብዛኛዎቹን ወንጀሎች የሚያካትት በመሆኑ - የሚሰጠው ምህረት ህገመንግስቱን የሚጥስ አለመሆኑን ማረጋገጥ ያስፈልጋል።

በህገመንግስቱ አንቀጽ 28 ላይ ምህረት የማይሰጥባቸው ወንጀሎች ተብለው የተዘረዘሩት ድርጊቶች በይዘታቸው አለምአቀፍ ወንጀሎች ተብለው የሚወሰዱ የወንጀል አይነቶች ናቸው። በአለምአቀፍ ደረጃም ለነዚህ ወንጀሎች

[4] ለምሳሌ የሰው ዘር ማጥፋት ወንጀል፡ ያለፍርድ ሞት ቅጣት እርምጃ የመውሰድ፡ በአስገዳጅ ሰውን መሰወር እና ኢሰብአዊ ድብደባ፡



Draft

ምሕረት መስጠት - በተለይም በቅድመ-ሁኔታ ላይ ያልተመሰረተ ምህረት መስጠት ላይ - ክልከላ/ገደቦች ተቀምጠዋል። ይሁንና እነዚህ ክልከላዎች በአመዛኙ ከግምት ያስገቡት የመደበኛ ጊዜ ሁኔታን እንጂ በሽግግር ላይ ያለ ማህበረሰብን ወይም ሀገራትን አይደለም። በመሆኑም በሽግግር ፍትህ የሀገራት የመክሰስ ተቀዳሚ ግዴታ - ከሀገራቱ መፍትሄ የመስጠት፡ ጥሰቶች ሲከሰቱም የማስወገድ፡ እና ድጋሚ እንዳይከሰቱ ዋስትና የመስጠት ግዴታችውን በሚያስቀር ወይም በሚያውክ መልኩ ተፈፃሚ የሚደረግ መሆን የለበትም።

በመሆኑም የአፍሪካ የሽግግር ፍትህ ፖሊሲ በግልጽ እንዳስቀመጠው - በሽግግር ላይ ያሉ ሀገራት ከመተግበር የሚከለከሉት - የተጎጂዎችን ፍትህ የማግኘት እና እውነትን የማወቅ መብት የሚገድቡ ያለምንም ቅድመ-ሁኔታ በደፈና የሚሰጡ የምህረት አይነቶችን ብቻ እንደሆነ ሊታወቅ ይገባል። ከዚህ ውጭ - የተጎጂዎችን ፍላጎት ባካተተ መልኩ - እውነትን፡ እርቅን እና ፍትህን ለማስፈን የሚረዳ - በቅድመ-ሁኔታ ላይ የተመሰረተ ምህረት እንደ አንድ የሽግግር ፍትህ እውቅና የተሰጠው ጉዳይ ነው።

በመሆኑም በህገ-መንግስቱ የተቀመጠው ክልከላም ሆነ የአለምአቀፍ ህጎች አጠቃላይ ይዘት - የተወሰነ ክፍተትን ወይም ተለዋዋጭነትን የሚፈቅድ ነው። እውነትን የማወቅ፡ የተበዳዮችን ማካካሻ የማግኘት መብትን አስከብሮ፡ እና ተጠያቂነትን አረጋግጦ በቅደመ-ሁኔታ የሚሰጥ ምህረት ስርአትን አገራት ሀገራት ሊቀርጹ ይችላሉ።

ከዚህ አንፃር - የአለምአቀፉ ህግም ሆነ የአፍሪካ የሽግግር ፍትህ ፖሊሲ በቅደመ-ሁኔታ የሚሰጥ ምህረትን የማይኮንኑ፡ እንደውም በሽግግር ፍትህ ሂደት ውስጥ የሚተገበር አንዱ መሳሪያ አድርገው የሚያስቀምጡ በመሆኑ - የህገ-መንግስቱን ድንጋጌ ይዘት በዚህ አግባብ አስማምቶ መረዳት ተገቢ ይሆናል።

## 2.7. ማካካሻ

### 2.7.1. ጠቅላላ

በሽግግር ፍትህ ሂደት - ማካካሻ - ለደረሱ የመብት ጥሰቶች ወይም የሐብት ውድመቶች ውጤታማና ተመጣጣኝ የገንዘብ ወይም ገንዘብ ያልሆነ ካሳ፡ መጠገኛ፡ ማደሻ ወይም ወደነበረበት ሁኔታ የመመለሻ መንገዶችን የያዘ ስልት ነው። የማካካሻ ፍትህ ዓላማ የተበዳዮችን ጉዳት መፈወስ እና የአጥፊዎችን ባህሪ ማስተካከል ነው።

በሙሉ ሊባል በሚችል መልኩ - በሀገራችን የተሞከሩ የፍትህ ሂደቶች የሰብአዊ መብት ጥሰት ተጎጂዎች ማካካሻ የማግኘት መብትን ባስከበረ መልኩ ባለመዘርጋታቸው - በተጎጂዎችና በህብረተሰቡ የፍትህ መጓደል ስሜትን ፈጥረዋል፡ ፡ የተሳካ እና ተቀባይነት ያለው የሽግግር ፍትህ ሂደት ለማከናወን - ማካካሻን ሰፋ አድርጎ በመመልከት፡ ተገቢውን ትኩረት ሰጥቶ ፖሊሲ በመንደፍ፡ ሀብት በማሰባሰብና በመመደብ፡ የተለያዩ አማራጮችን በመጠቀም፡ በቂ ውጤታማ እና ፈጣን የማካካሻ ስርአት መገንባት ያስፈልጋል።

### 2.7.2. በማካካሻ ስርአቱ ምን አይነት የማካካሻ አይነቶች ሊተገበሩ ይችላሉ?

**ወደነበረበት ሁኔታ መመለስ፡-**

ይህ አካሄድ ተጎጂዎችን ከጉልህ የሰብአዊ መብት ጥሰት በፊት ወደነበሩበት ሁኔታ መመለስን አላማው የሚያደርግ ነው። ሰዎች ወደተፈናቀሉበት ቦታ የመመለስን፡ ያጡትን የስራ እድል ወይም የጠፋ ወይም የተወሰደ ሐብት፡ ይዞታ፡ እና/ወይም ባለንብረትነትን የመመለስ ስራን ያካትታል። ይህ ሂደት በዋናነት የመንግስትን 'ህላፊነት የመወጣት መደበኛ ተግባርን' እንጂ ተጨማሪ ወጪን እንደሚጠይቅ ስራ ተደርጎ መታሰብ የለበትም።

**ካሳ፡-**

ይህ ሂደት ተጎጂዎች ለደረሰባቸው የመብት ጥሰትና ጉዳት ተመጣጣኝ የሆነ ቁሳዊ ወይም የገንዘብ ካሳ መስጠትን ያካትታል። በግጭት የወደመ ሐብትን መልሶ መገንባትን፡ እንዲሁም የስራ እድል፡ ጡረታ እና የገንዘብ ካሳ መስጠትን ሊያጠቃልል ይችላል። በዚህ ረገድ የሚመከረው አካሄድ መንግስት የሚመድበው በጀት እንደተጠበቀ ሆኖ - ጥፋት

*ፈፃሚዎች እና በነበረው ሁኔታ ተጠቃሚ የሆኑ ሰዎች ለካሳ እና መልሶ ማቋቋሚያ ፕግራሞች የበኩላቸውን አስተዋፅዖ እንዲያደርጉ ማድረግ ተገቢ መሆኑን ነው።*

***የጋራ ካሳ፡-***

*የጋራ ካሳ - የማሕበረሰብ ወይም የጋራ መሬቶችን መመለስን፣ የጤና የትምሕርት የፀጥታ የፍትሕ እንዲሁም የሌሎች የሕዝብ አገልግሎት መሰረተ-ልማቶችን መልሶ መገንባትን፣ እና የሕጻናትና ወጣቶች ጥቅምን ባገናዘበ መልኩ የተጎዱ ማሕበረሰቦች የእለት-ተእለት-ኑሮ መሰረት የሆኑ መዋቅሮችንና ሥርአቶችን መልሶ መገንባትን፣ እንዲሁም በገንዘብ ወይም በአገልግሎት መልክ ለማሕበረሰቡ ካሳ መስጠትን ያካትታል።*

***መታሰቢያ፡-***

*ይህ ሂደት - የማስታወሻ ክዋኔዎችን ማድረግ፣ ሐውልትና ምልክቶችን ማቆም፣ የሕዝብ መሰብሰቢያ ቦታዎችንና ሕንፃዎችን እንደገና መሰየምን፣ ኪነ-ጥበባዊና የባህል መገለጫዎችን እንዲሁም ብሔራዊ አርማዎችንና ሕዝባዊ በአላትን እንደገና መቃኘትን፣ እና/ወይም የታሪክ መጻሕፍትንና ሥርአተ-ትምሕርትን ማሻሻልን ሊጨምር ይችላል።*

***እርካታ፡-***

*ይህ ስራ ተጎጂዎች እና ቤተሰቦቻቸው ስለደረሰባቸው ሞት፣ ስቃይ ወይም በደል እውነተኛ መረጃ ማውጣትን፣ ለጥሰቶች ሕዝባዊ እውቅና መስጠትን፣ ለጥፋት ይቅርታ መጠየቅን፣ እና ለመታሰቢያቸው ድጋፍ ማድረግን ጨምሮ - ቁሳዊ ያልሆኑ ካሳዎችን የሚመለከቱ ተግባራትን ሁሉ ያጠቃልላል።*

***ማገገም፡-***

*ማገገም የሕክምና፣ የሥነ-ልቦና እና መሰል አገልግሎቶችን፣ እንዲሁም ተጎጂ-ተኮር-ድጋፎችን መስጠትን ጨምሮ - መሰረታዊ አገልግሎቶችን በልዩ ትኩረት ማቅረብን ያጠቃልላል።*

***እንዳይደገም ማድረግ፡-***

*ተመሳሳይ የሰብአዊ መብት ጥሰቶች እና ሌሎች በደሎችን ለመከላከል እና እንዳይደገሙ ዋስትና ለመስጠት ያስችል ዘንድ - ጥሰቶቹ እንዲፈጸሙ ያስቻሉ የህግ ማዕቀፎችን እና ተቋማትን በተገቢው መልክ መለወጥ፣ የግጭት ቅድመ ትንበያ፣ መከላከል እና መቆጣጠር ዘዴዎችን ማሳደግ፣ እና ጥሰቶች እንዳይደገሙ ለማድረግ የሚረዱ ሌሎች አውድ ተኮር ዘዴዎችን መተግበርን ያጠቃልላል።*

### 2.7.3. *የማካካሻ ስርአት ለመገንባት የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት*

**የማካካሻ ስርአቱን በሚመለከት የህግ ማእቀፍ እንዲኖር ማድረግ፡**

በሀገራችን - የከፍተኛ ሰብአዊ መብት ጥሰት ተጎጂዎች የማካካሻ ስርአት በህግ ሊደነገግ ይገባል። በህግ የማካካሻ ስርአቱን ባህሪ እና ይዘት፣ የካሳ ክፍያ ሁኔታዎች፣ እንዲሁም በተጎጂዎች ትርጉም እና ተዛማጅ ጉዳዮች ላይ ድንጋጌዎችን በማስቀመጥ - መንግስት ግዴታ ኖሮበት በቁርጠኝነት እንዲሰራ ማድረግ ያስፈልጋል።

**በግል ካሳ የሚሰጣቸው ተበዳዮችን መለየት፡**

በማካካሻ አፈጻጸም ሂደት ማካካሻ በማን ላይ ተፈጻሚ እንደሚሆን መለየት ቁልፍ ነጥብ ነው። ይህም በሽግግር ፍትህ ሂደት ተጎጂ ወይም ተበዳይ ማን ወይም እነማንን እንደሚያካትት መለየትን ይጠይቃል። ለሁሉም ተጎጂዎች የግል ካሳ መስጠት የሚያስችል ስርአት መገንባት የሚቻል ባለመሆኑ - ተገቢ የማጣራት እና የልየታ ተግባራትን ማከናወን ያስፈልጋል።

**በማካካሻ ስርአት ጥፋት ፈፃሚዎች ሀላፊነት የሚወስዱበትን መንገድ መለየት፡**

Draft

ስኬታማ በሚባሉ የሽግግር ፍትህ የማካካሻ ፕሮግራሞችን ሞዴል በመከተል - ጥፋት ፈፃሚዎች የሚኖርባቸው ሀላፊነት እውነታውን በማውጣት እና ይቅርታ በመጠየቅ ብቻ የተወሰነ ሳይሆን - እንደ አግባብነቱ ላደረሱት ጉዳት እንዲክሱ፣ ያጠፉትን እንዲመልሱ፣ እንዲሁም ካሳ በመክፈል ረገድ ሀላፊነት እንዲኖርባቸው ስርአት ዘርግቶ መተግበር ያስፈልጋል፡ ፡

**የተጎጂዎች ፈንድ ማቋቋም፣**

እንደ ኢትዮጵያ ባሉ ውስን የኢኮኖሚ አቅም ባላቸው ሀገራት የሰብአዊ መብት ጥሰት ለሚደርስባቸው ሰዎች - ዓለምአቀፍ የሰብአዊ መብት ድንጋጌዎች በሚያስቀምጡት ግዴታ መሰረት - ሰዎችን ወጥ እና በቂ በሆነ መንገድ መልሶ ለማቋቋም እና ለመካስ የሚያስችል የተጎጂዎች ፈንድ ማቋቋም - ሀብት ለመመደብም ሆነ ለመሰብሰብ ጠቃሚ አካሄድ እንደሆነ ታይቷል። ስለሆነም ከላይ በተጠቀሰው የህግ ማእቀፍ - ለተገቢው አካል ስልጣን እና ሀላፊነት በመስጠት - ይህን አይነት ፈንድ ማቋቋም አስፈላጊ ይሆናል። ፈንድ የሚቋቋመው በህግ በመሆኑ - ከላይ የካሳ ስርአትን በህግ መደንገግ እንደሚያስፈልግ ከተገለጸው ነጥብ ጋር አያይዞ በአንድ ህግ ማውጣት ይቻላል።

## 2.7.4. ተቋማዊ ጉዳዮች፡- የማካካሻ ስርአትን ማን ይመራዋል/ያስተባብረዋል?

የማካካሻ ስርአትን በዋነኝነት የሚመራው ወይም የሚያስተባብረው ማን መሆን አለበት? ማካካሻ እንዴት እና በማን ይሰጣል የሚለውን በሚመለከት - የሚከተሉትን ተቋማዊ አማራጮች መጠቀም ይቻላል።

**አማራጭ አንድ፣ አዲስ በሚቋቋም ኮሚሽን አማካኝነት ማከናወን፣**

በሌሎች ሀገሮች ልምድ እንደታየው በሽግግር ፍትህ ሂደት የማካካሻ ስርአቱን በባለቤትነት የመምራት፣ የማስተባበር፣ ማካካሻ ለማን እና እንዴት መሰጠት እንዳለበት የመለየት፣ እንዲሁም በጋራ የማካካሻ መንገዶች ላይ ምክረ-ሀሳብ የመስጠት ስልጣን እና ሀላፊነት - በሂደቱ ለሚቋቋሙ የእውነት፣ የእርቅ እና የማካካሻ ኮሚሽኖች የሚሰጥ ተግባር ነው። በኢትዮጵያም አንደኛው አማራጭ ይህንን ተግባር ነጻና ገለልተኛ ሆኖ ለሚቋቋም የእውነት እና የእርቅ ኮሚሽን መስጠት ነው። ኮሚሽኑም ለዚሁ ተግባር የሚቋቋመውን የተጎጂዎች ፈንድ መጠቀም የሚችልበት የህግ ማእቀፍ ይኖረዋል።

**ጠንካራ ጎኖች**

- ለተጎጂዎች ተፈጻሚ የሚሆን ውጤታማ የማካካሻ መርሀ-ግብር መቅረጽ ውስብስብ፣ ሰፊ እቅድ እና ማስተባበርን የሚጠይቅ ስራ ነው፣ ይህን ተግባራዊ ለማድረግ ራሱን የቻለ ኮሚሽን በማቋቋም ወደ ስራ መግባት ስራው የበለጠ ውጤታማ እንዲሆን ያደርጋል፣
- ኮሚሽኑ ሌሎች ተግባራቶቹን ሲከውን የተጎጂዎችን እና አጥፊዎችን ማንነት እና ሁኔታ ለይቶና መዝግቦ የሚያዝ በመሆኑ፣ በተለይም ይህ መረጃ ማካካሻ ሊሰጣቸው የሚገቡ ተጎጂዎችን፣ ሊሰጥ የሚገባው የማካካሻ አይነትና መጠንን፣ እንዲሁም የአጥፊዎችን ተሳትፎ መጠን ለመወሰን ስለሚያስችለው የበለጠ ውጤታማ ያደርገዋል፣
- እነዚህ ተቋማት ካላቸው ነጻነትና ገለልተኛነት በተጨማሪ በሂደታቸው ማህበረሰቡን የሚያሳተፉ በመሆኑ ተአማኒነቱ ከፍ ያለ ይሆናል፣

**ስጋቶች**

- በሀገር ካለው ውስን ሀብት አንፃር ኮሚሽን ማቋቋም ከፍተኛ ወጪ የሚጠይቅ ነው፣
- አዲስ ኮሚሽን ማቋቋም ከዚህ ቀደም ተሞክሮ የነበረ በመሆኑ የፖለቲካ ተነሳሽነቱ ዝቅተኛ ሊሆን ይችላል፣

- ከሀገሪቱ የቆዳ ስፋት፡ ከሂደቱ ጥልቀት እና ኮሚሽኑ ከሚኖረው የጊዜ ገደብ አንፃር የተደራሽነት ችግር ሊኖር ይችላል፡
- ማካካሻ በራሱ የሚፈልገው ብቃት እና የማስተዳደር አቅም (ለምሳሌ የካሳ መጠንን መወሰን) የተለየ በመሆኑ ኮሚሽኑ ተግባራቱን ለማከናወን የሚስችለውን አደረጃጀት መወሰን አስቸጋሪ ሊሆን ይችላል፡
- በሀገሪቱ ካለው አስፈላጊነት አንፃር የካሳን ጉዳይ የሚመለከት ስልጣን በጊዜ ለተገደበ ኮሚሽን መስጠት ቀጣይነት እንዳኖረው ያደርጋል፡

**አማራጭ ሁለት፡** የግል ካሳ ጉዳይን በመደበኛው የህግ ስርአት በፍርድ ቤቶች እንዲታይ መተው፡ በጋራ ማካካሻ ጉዳዮች ላይ ተገቢ የህግ ማሻሻያ በማድረግ - የማካካሻ ስርአቱን ስራ በሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን ወይም በኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን አማካኝነት እንዲፈፀም ማድረግ።

**ጠንካራ ጎኖች**

- አሁን ያሉ ተቋማትን በመጠቀም በሀገር ያለውን ውስን ሀብት ይቆጥባል፡
- ተቋማዊ አቅምን ይገነባል፡ ቀጣይነት እንዲኖር ያስችላል፡
- በፍትህብሄር ህጉ መሰረት የሰብአዊ መብት ጥሰት በፈፀሙ ግለሰቦች ላይ የግል ተጠያቂነት እንዲኖር በማድረግ ግለሰባዊ ሀላፊነትን ይበልጥ ያረጋግጣል፡

**ስጋቶች**

- ተቋማቱ በሽግግር ፍትህ ሂደት የማካካሻ ስርአትን ውስብስብ ስራ ለመተግበር የሚያስችል አቅም የላቸውም፡
- የማካካሻ ስርአቱን በሽግግር ፍትህ ስርአት ተግባር ላይ ከሚውሉ ሌሎች መንገዶች ጋር ለማቀናጀት አስቸጋሪ ያደርገዋል፡
- የተጎጂዎች ማካካሻ የማግኘት መብትን በመደበኛ የህግ ስርአት ለማስፈፀም መሞከር በመደበኛ ጊዜም ጭምር አዳጋች በመሆኑ ውጤታማ ላይሆን ይችላል፡
- ሁለቱም ተቋማት ከፍተኛ ሀላፊነት እና መጠነ-ሰፊ ተግባራት ያላቸው በመሆኑ የማካካሻ ስርአትን ከፍተኛ የስራ ጫና በውጤታማነት ላያከናውኑት ይችላሉ፡
- ሁሉም ጉዳዮች በፍርድ ቤት ስርአት ላያልፉ ስለሚችሉ በተጎጂዎች መካከል ልዩነት እንዲኖር ያደርጋል፡

## 2.8. ተቋማዊ ማሻሻያ

### 2.8.1. ጠቅላላ

በሽግግር ፍትህ ሂደት አንድ ሀገር - ከእርስ በእርስ ግጭት፡ ጦርነት ወይንም ጭቆና መላቀቅ በኋላ - ከፍተኛ የሰብዓዊ መብት ጥቃት ያደረሱ ወይም አድርሰዋል ተብለው የሚታሙኑ ሰዎችን በሀላፊነት ቦታ ህዝብን እንዲያገለግሉ ማድረግ - ለሚታሰበው የእርቅ እና የሰላም ሂደት እንቅፋት ይፈጥራል። ስለሆነም - ተገቢ ፖሊሲ እና ስትራቴጂ በመቅረፅ በእንዲህ አይነት ተግባር ላይ ተሰማርተው የነበሩ የመንግስት ሀላፊዎችንና ሰራተኞች መለየት፡ ማጣራት እና ከስራ በማሰናበት ወይም አንደ አስፈላጊነቱ በሌላ ቦታ እንዲሰሩ በማድረግ ተቋማዊ ማሻሻያ ማድረግ ይጠበቃል። ይህም ተቋማቱን በተገቢዉ መልኩ ለመቀየርና የተቋማቱን ተአማኒነት፡ ቅቡልነት እና አሰራር በመለወጥ ዘላቂ የሆነ ማሻሻያ እንዲኖር መሰረት ይጥላል።

በኢትዮጵያ በ2010 ዓ.ም. ከተደረገው የመንግስት ለውጥ በኋላም የቀጠሉት ተቋማት እና ግለሰቦች በአብዛኛው ከለውጡ በፊት የነበሩ ናቸው። ስለሆነም በሚታሰበው የሽግግር ፍትህ ሂደት ጉልህ የሰብአዊ መብቶች ጥሰት የፈፀሙ፣ ወይም ጥሰቶቹ ሲፈፀሙ በአንድ ሆነ በሌላ መልኩ የተሳተፉ ሰዎችን በተመሳሳይ ሁኔታ እንዳይቀጥሉ ማድረግ ያስፈልጋል። እንዲሁም የተሳካ የሽግግር ፍትህ እንዲኖር እና ጥሰቶች እንዳይደገሙ ለማድረግ የተቋማት ማሻሻያን እንደ አንድ የሽግግር ጊዜ መፍትሄ መተግበር ያስፈልጋል።

### 2.8.2. በሽግግር ፍትህ ሂደት የተቋማዊ ማሻሻያ ተግባራት ምን ምን ሊያካትቱ ይችላሉ?

**መለየት እና ማጥራት፣**

ይህ ስራ በተቋማዊ ማሻሻያ ትኩረት የሚሰጣቸውን ተቋማት፣ የስራ ክፍሎች እና ግለሰቦች በአግባቡ በመለየት - ግልጽ በሆነ የልየታ ሂደት የሰብአዊ መብቶች ረገጣና ግፍ ሲፈጽሙና ሲያስፈፅሙ የነበሩ የመንግስት ባለስልጣናት፣ ሀላፊዎች እና ሰራተኞችን የመለየት እና የማጣራት ሂደት የሚያካትት ነው። ይህ አይነቱ ሂደት የዘፈቀደ እና ህገወጥ ሂደት እንዳይሆን - የፍትህ ሂደት መስፈርቶችን እና የአለምአቀፍ የሰብአዊ መብት መስፈርቶችን ባከበረ መልኩ መከናወን ይኖርበታል።

**ከስራ እና ከሀላፊነት ማግለል፣**

ይህ ሂደት - ላለፉ ጉልህ የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶች አስተዋጽኦ አላቸው ተብለው የተለዩ ግለሰቦችን - ተገቢ በሆነ የማጥራት ሂደት በመለየት - ከስራ እና ከሀላፊነት የማንሳት ሂደት ነው። ይህም በአንድ ጎኑ ጥፋት አጥፍቶ ነፃ የሚኮንበትን መንገድ ለማጥበብ ስራ ላይ የሚውል አካሄድ ሲሆን፤ በሌላ ጎኑ በጥፋት ላይ ተሰማርቶ የነበረን የመንግስት ባለስልጣን እና ሰራተኛ ከቢሮውና ከስራው በማግለል - በበደለው ሰው ፊት ስራውን እየሰራ እንዳይቀጥል በማድረግ - እንደ አንድ ማካካሻ ለእርቅና ሰላም አስተዋፅኦ የሚያደርግ አካሄድ ነው።

**የህግ እና የአሰራር ለውጥ፣**

የዚህ አላማ - ሁሉም ተቋማት የህግ፣ የመዋቅር እና የሰው ሀይል ማሻሻያዎችን ተግባራዊ በማድረግ የዜጎችን መብት የሚያከብሩ፣ የሚያስከብሩ እና ያለፉትን አይነት የሰብአዊ መብት ጥሰቶች እንዳይደገሙ ለመከላከል የሚያስችሉ ህጎች፣ አደረጃጀቶች እና አሰራሮችን መፍጠር ነው።

### 2.8.3. ተቋማዊ ጉዳዮች፡- የተቋማዊ ማሻሻያ ተግባራቱ በማን ይከናወናሉ?

የልየታ፣ የማጥራት እና ከስራ የማግለል ተግባራት በከፍተኛ ጥንቃቄ መከናወን ያለባቸው ስራዎች ናቸው። ሂደቱ ፍትህን በማዛባት ተከናውኖ ሰዎች እንዳይበደሉ፣ በሚወሰደው እርምጃም በመንግስታዊ ስራ ላይ ክፍተት ተፈጥሮ አገልግሎት እንዳይጓደል፣ እንዲሁም የማግለሉ ሂደት የሁከት ምንጭ እንዳይሆን - በንቃት እና በጥንቃቄ ደረጃ በደረጃ መከናወን አለበት። በዚህ ረገድ ሁለት አማራጮችን መመልከት ይቻላል።

**አማራጭ አንድ፣ የተቋማትን ለውጥ የሚያስተገብር የልየታ፣ የማጥራት እና ከስራ የማግለል ስልጣን የተሰጠው ገለልተኛና ነጻ የሆነ አካል በማቋቋም ተግባራቶቹን ማከናወን፣**

በዚህ አማራጭ መንግስት የልየታ፣ የማጥራት እና ከስራ ማግለል ሂደቱ የሚመራበት ግልጽ የሆነ ስነ-ስርአት በማስቀመጥ በኮሚሽን/በኮሚቴ ወይም በፅ/ቤት ደረጃ የሚደራጅ አካል በማቋቋም ተግባራቱን የማከናወን አማራጭ ነው።

**ጠንካራ ጎኖች**

- የማጥራት ሂደቱን በነፃነት እና በገለልተኝነት የመከናወን እድል ያሰፋል፣ ቅቡልነቱንም ይጨምራል፣
- ፖለቲካዊ እና ኢ-መደበኛ የሆኑ የጎሳ እና የብሄር ቡድኖች ጣልቃ ገብነትን ለመከላከል ያስችላል፣

Draft

- ከሌሎች የሽግግር ፍትህ መንገዶች ጋር ያለውን መስተጋብር የበለጠ ጠንካራ ያደርገዋል፡

**ስጋቶች**

- በሀገር ካለው ውስን ሀብት አንፃር ሌላ አካል ማቋቋም ከፍተኛ ወጪ የሚጠይቅ ነው፡
- በሀገራችን ካለው ነባራዊ ሁኔታ አንፃር የልየታ እና የማጥራት ተግባርን በስኬት ለማከናወን የሚያስችል ፖለቲካዊ ቁመና ላይኖረው ይችላል፡

**አማራጭ ሁለት፡ በሁሉም ተቋማት ውስጥ የልየታ፣ የማጥራት እና ከስራ የማግለል ሀላፊነት ያላቸው ቡድኖችን በማዋቀር ተግባራቶቹን ማከናወን፡**

ይህ አማራጭ መንግስት የልየታ፣ የማጥራት እና ከስራ የማግለል ሂደቱ የሚመራበትን ግልጽ ስነ-ስርአት በማስቀመጥ - ተቋማዊ ማሻሻያ ለማድረግ - ደረጃ በደረጃ በሚመረጡ ተቋማት ውስጥ - ነፃ እና ገለልተኛ ሆነው የሚቋቋሙ ቡድኖችን በማደራጀት ተግባራቱን የማከናወን ሂደትን የሚመለከት ነው።

**ጠንካራ ጎኖች**

- ሂደቱ አሁን ባሉ ተቋማት ውስጥ እንዲከናወን በማድረግ በሀገር ያለውን ውስን ሀብት ይቆጥባል፡
- ተቋማዊ አቅምን ይገነባል፡ ቀጣይነት እንዲኖር ያስችለዋል፡
- በተቋማቱ ባለቤትነት እንዲመራ፣ ተገቢ የፖለቲካ ቁመና እንዲኖረው እና ሊመጡ የሚችሉ ስጋቶችን በቅርበት በማወቅ መፍትሄ ለመስጠት ያመቻል፡

**ስጋቶች**

- ሂደቱ በነፃነት እና በገለልተኝነት የመከናወን እድሉን ያጠበዋል፡ የቅቡልነት ፈተና ይፈጥራል፡
- በሽግግር ፍትህ ሂደት በሚፈለገው መጠን አለማቀፋዊ መስፈርቶችን በመጠቀም የማከናወን አቅም እና ፍላጎት ላይኖር ይችላል፡
- ከእውነተኛ ማጥራት እና ማግለል ይልቅ ክፍተት እና ግጭት እንዳይፈጠር በመስጋት ፖለቲካን መሰረት ያደረጉ ውሳኔዎች የማሳለፍ እድልን ይጨምራል፡

## 2.9. ውሳኔ የሚያስፈልጋቸው ጉዳዮች

በኢትዮጵያ ለሚታሰበው የሽግግር ፍትህ ፖሊሲ እና ሂደት - ከላይ በተዘረዘሩት መንገዶች ላይ ከሚነሱ ጉዳዮች በተጨማሪ - አቅጣጫ እና ውሳኔ የሚያስፈልጋቸው ጉዳዮች አሉ። እነዚህም የሚከተሉትን ይጨምራሉ።

### 2.9.1. የሽግግር ፍትህ ሂደቱ ከየትኛው ጊዜ ይጀምር?

ስኬታማ በሆኑ የሽግግር ፍትህ ሂደቶች የታየው አንዱ ጠቃሚ አካሄድ - በሂደቱ የሚሸፈነውን የጊዜ መነሻ እና መዳረሻ መወሰን ነው። ሂደቱ እጅግ የራቀ የመነሻ ጊዜ ኖሮት - ወሰኑ እጅግ እንዲሰፋ፣ እና ማስረጃ እና ምስክሮች በማይገኙበት ጊዜ እንዲጀምር ማድረግ ስራው ውጤታማ እንዳይሆን ያደርገዋል። በሌላ በኩል በጣም የቀረበ የመነሻ ጊዜ ኖሮት ዋና ዋና የሰብአዊ መብት ጥሰቶች የተከሰቱበትን ጊዜ የማያካትት ከሆነ - የታሰበለትን አላማ ለማሳካት አይችልም። ስለሆነም በሀገራችን ለመተግበር በሚታሰበው ሂደት - ሀገራዊ አውዱን ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት - የጊዜ ወሰኑን ማስቀመጥ ያስፈልጋል።

Draft

መዳረሻን በሚመለከት ያለው አማራጭ ፖሊሲው ፀድቀ ወደስራ እስከሚገባበት ጊዜ ያለውን ጊዜ በሙሉ እንዲሸፍን ማድረግ ነው። በዚህ ሰነድ ክፍል አንድ - ከለውጡ በኋላም ቢሆን ተስፋፍቶ በቀጠለው ግጭት እና የእርስ በርስ ጦርነት መጠነ-ሰፊ የሰብአዊ መብት ጥሰት መኖሩ እና ከለውጡ በኋላ የተሞከሩት የሽግግር ፍትህ ሂደቶችም ስኬታማ ያልነበሩ መሆናቸው ተመላክቷል። ስለሆነም ዓላማውን ሊያሳካ የሚችል የሽግግር ፍትህ ሂደት እንዲኖር ካስፈለገ መዳረሻው በቅርቡ የተከሰቱ የመብት ጥሰት ሁኔታዎችን ሊያካትት ይገባል።

መነሻ ጊዜውን በሚመለከት የሚከተሉትን አማራጮች መመልከት ይቻላል።

**ከ1983 በፊት ያለ ጊዜ፡**

በሀገራችን ታሪክ - በሽግግር ፍትህ አውድ - ይቅርታ፡ እውነት እና ምህረት ያስፈልጋቸዋል ተብለው የሚታሰቡ በተለያየ ጊዜ የተፈፀሙ በርካታ እና መጠነ ሰፊ ጥሰቶች እንዳሉ የሚታወቅ ነው። አንዳንዶች ራቅ ብለው ይህ ጊዜ ከአጼ ሚኒሊክ ሁለተኛ ዘመነ-መንግስት መጀመር አለበት ሲሉ፡ ሌሎች ከአፄ ሀይለስላሴ፡ ሌሎች ደግሞ አብዮቱ ከፈነዳበት ከ1966 ዓ.ም ጀምሮ ሊሆን ይገባል ይላሉ። በዚህ አማራጭ - የሽግግር ፍትህ ሂደቱ ከዚያ እንዲጀምር ይደረጋል።

**ጠንካራ ጎኖች**

- ሲንከባለሉ የመጡ እና ረጅም ጊዜ ያስቀጠሩ የተዛቡ ታሪካዊ አረዳዶችን እና ጥሰቶችን በማካተት ከስረ መሰረታቸው ለመፍታት፡ በይቅርታ እና እርቀ ወደፊት ለመራመድ የሚያችል ሰፊ የጊዜ ወሰን እንዲኖር ያስችላል፡

**ስጋቶች**

- ክስተቶቹ ረጅም ጊዜ ከማሳለፋቸው አንፃር ተጎጂዎችን እና ምስክሮች የማግኘት ተግባር አስቸጋሪ ይሆናል፡
- ታሪካዊ አረዳዶች ወይም ትውስታዎች የተዛቡ እና የተበረዙ የመሆን እድላቸው የሰፋ ነው፡
- አሁን ላለንበት ወቅት አስፈላጊ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ትኩረት እንዳይሰጥ በማድረግ ሂደቱ ውጤታማ እንዳይሆን ያደርጋል፡
- ረጅም ሂደቶችን ማየት የሚፈልግ በመሆኑ በአጭር ጊዜ ለማጠናቀቅ የሚቻል አይደለም፡
- በቀደሙ ጊዜያት በነበሩ ታሪኮች እና ጉዳዮች ላይ በቀላሉ መግባባት ላይ መድረስ ያዳግታል፡
- ረጅም ጊዜ የወሰዱ ታሪካዊ ጥሰቶች እና ጉዳዮች ከሽግግር ፍትህ ሂደት ይልቅ በብሄራዊ ምክክር አውድ ቢታዩ የተሻለ ውጤት ሊያስገኙ ይችላሉ።

**ከ1983 ጀምሮ ያለ ጊዜ፡**

ይህ አማራጭ የሽግግር ፍትህ ሂደቱን - የኢህአዴግ መንግስት አዲስ አበባን ከተቆጣጠረበት ከግንቦት 20 ቀን 1983 ዓ.ም ጀምሮ እንዲሆን ያደርገዋል። በተለይም ጊዜው ሰብአዊ መብቶችን ያካተተ የሽግግር መንግስት ቻርተር የተረቀቀበት እና በኢትዮጵያ የፖለቲካ ታሪክ አዲስ ምእራፍ የተጀመረበት ወቅት ከመሆኑ አንፃር ተገቢ ሊሆን ይችላል። ይህ አማራጭ የሚከተሉት ጠንካራ እና ደካማ ጎኖች ይኖሩታል።

**ጠንካራ ጎኖች**

- የሽግግር ፍትህ ሂደቱ መካከለኛ የጊዜ ወሰን እንዲኖረው እና ለተቀጠሉት ታሪካዊ ክስተቶች እና ጥሰቶች መነሻ የሆኑ በሽግግሩ ጊዜ የተፈፀሙ ተግባራትን እንዲያካትት ያስችላል፡

Draft

- መረጃዎች እና ማስረጃዎችን ለማግኘት ቀላል ነው፡

- በአጭር ጊዜ ለማጠናቀቅ ያስችላል፡

**ስጋቶች**

- በተወሰነ ቡድን ወይም የህብረተሰብ ክፍል ላይ ያነጣጠረ ሂደት ሊያስመስለው ይችላል፡ ይህም ቅሬታን ያስነሳል፡

- በሽግግር መንግስቱ ወቅት የተከወኑ ጥሰቶችን እንዲያካትት በማድረግ፡ ሰላምና መረጋጋት ባልነበረበት እና ህገ-መንግስቱ ፀድቆ ግልፅ ግዴታዎች ባልተመሰረቱበት ወቅት ጭምር የሽግግር ፍትህ ሂደቱ እንዲጀምር ማድረግ ጥያቄ እንዲነሳበት ያደርጋል፡

**ከ1987 ጀምሮ ያለ ጊዜ፡**

ይህ ጊዜ የሽግግር መንግስቱ ዘመን ተጠናቀ - ሀገሪቱ የምትተዳደርበት ሕገ-መንግስት የፀደቀበት፡ በህገ-መንግስቱ አንቀፅ 9(2) መሰረትም - ሰብአዊ መብቶችን ጨምሮ ሕገ-መንግሥቱን የማክበር፡ የማስከበር እና የማሟላት የመንግሥት ሃላፊነት በይፋ የተደነገገበት ወቅት በመሆኑ ተገቢ ሊሆን ይችላል። ይህ አማራጭ የሚከተሉት ጠንካራ እና ደካማ ጎኖች ይኖሩታል።

**ጠንካራ ጎኖች**

- ሰብአዊ መብቶችን የማክበር፡ የማስከበር እና የማሟላት የመንግስት ግዴታ ከተደነገገበት ጊዜ እንዲጀምር በማድረግ ለነበሩት ጥሰቶች ጠንካራ ህጋዊ መሰረት ይሰጣል፡

- የተቋማት፡ የአመራሮች እና ባለሙያዎች ተግባርና ኃላፊነት በግልፅ የተለየበት ወቅት በመሆኑ ተጠያቂነትን ለማረጋገጥ ቀላል ነው፡

- መረጃዎችንና ማስረጃዎችን ለማሰባሰብ የቀለለ ነው፡

- ሂደቱን በአጭር ጊዜ ውስጥ ማጠናቀቅ ይቻላል፡

**ስጋቶች**

- ሂደቱ በተወሰነ ቡድን ወይም የህብረተሰብ ክፍል ላይ ያነጣጠረ ነው የሚል ቅሬታ ሊያስነሳ ይችላል፡

- ከህገ-መንግስቱ በፊትም ሆነ በኋላ መንግስት የሆነው ኢህአዲግ ሆኖ ሳለ የሽግግር መንግስት ወቅቱን አለማካተት በተጎጂዎች ላይ የፍትህ መጓደል ስሜት በመፍጠር በሂደቱ ቅቡልነት ላይ ጥያቄ ያስነሳል።

**ከ2010 ጀምሮ ያለ ጊዜ፡ ፡**

በመጋቢት ወር 2010 ዓ.ም. የመጣው የፖለቲካ ለውጥ ሌላ አዲስ ምእራፍ የተጀመረበት፡ አዲስ መንግስት ስልጣን ተቀብሎ ያለፉ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶችን በይፋ በማመን ይህንኑ ለማሻሻል ቃል የገባበት፡ የዲሞክራሲ ሽግግር ለማድረግ የሚስችሉ ተግባራትም የተጀመሩበት ወቅት በመሆኑ ተገቢ ሊሆን ይችላል። ይህ አማራጭ የሚከተሉት ጠንካራ እና ደካማ ጎኖች ይኖሩታል።

**ጠንካራ ጎኖች**

- ለሽግግር ፍትህ ሂደቱ ውስን የጊዜ ወሰን በመስጠት የተቀላጠፈ እና ፈጣን የሽግግር ጊዜ ፍትህ ሂደት እንዲኖር ያደርጋል፡

- *መረጃዎችንና ማስረጃዎችን ለማሰባሰብ የቀላለ ነው፡*

- *ሂደቱን በአጭር ጊዜ ማጠናቀቅ የሚቻልበት እድል የሰፋ ነው፡*

***ስጋቶች***

- *አብዛኞቹ ጥሰቶች ተንከባለው የመጡ ሆነው ሳለ የሽግግር ፍትህ ሂደቱ በጣም አጭር የጊዜ ወሰን እንዲኖረው ማድረግ በተጎጂዎች ዘንድ ከፍተኛ የፍትህ መጓደል ስሜት ይፈጥራል፡ የሽግግር ፍትህ ሂደቱ አላማዎችም በአብዛኛው እንዳይሳኩ ምክንያት ይሆናል፡*

- *የችግሮች ታሪካዊ አውድን ወደ ኋላ ተመልሶ በማየት ከስር-መሰረታቸው ለመፍታት አያስችልም፡*

- *በተወሰነ ቡድን ወይም የህብረተሰብ ክፍል ላይ ያነጣጠረ ሂደት ያስመስለዋል፡ ይህም ቅሬታን ያስነሳል፡*

***ለክስ ጉዳይ ከ1987 ጀምሮ፤ ለእርቅና ማካካሻ ጉዳይ ግን መረጃ እና ማስረጃ ከተገኘበት ጊዜ ጀምሮ፤***

*ክስን በተመለከተ ከአለም-አቀፍ ወንጀሎቹ ውጭ ያሉት የይርጋ ጊዜ አላቸው። ከፍተኛው የይርጋ ጊዜ 25 ዓመት ሲሆን፡ ከ1987 ዓ.ም ጀምሮ ያለው ጊዜ ሲቆጠር ከ25 አመት በላይ ስለሚሆን የወንጀሉ ጉዳይ በይርጋ የሚታገድ ይሆናል። ስለሆነም የወንጀል ጉዳይን በተመለከተ ከዚህ አመት ጀምሮ ቢሆን፡ እርቅ እና ሌሎች የሽግግር ፍትህ አላባዎችን በተመለከተ በመርህ ደረጃ ከላይ የቀረቡትን አማራጮች በማጤን መነሻ ጊዜን መበየን ተገቢ ቢሆንም - ለእርቅ አስፈላጊ እስከሆነ እና ማስረጃ እስከተገኘ ድረስ ወደኋላ እስከየትኛውም ጊዜ ድረስ በመሄድ ጉዳይን ማየት ይቻላል።*

***ጠንካራ ጎኖች***

- *መንግስት ሰብአዊ መብቶችን የማክበር፡ የማስከበር እና የማሟላት ግዴታ ከተደነገገበት ጊዜ እንዲጀምር በማድረግ ለነበሩት ጥሰቶች ጠንካራ ህጋዊ መሰረት ይሰጣል።*

- *የተቋማት፡ የአመራሮች እና የባለሙያዎች ተግባርና ኃላፊነት በግልፅ የተለየበት ወቅት በመሆኑ ተጠያቂነትን ለማረጋገጥ ቀላል ነው፡*

- *መረጃዎችንና ማስረጃዎችን ለማሰባሰብ ቀላል ነው፡*

- *ከወንጀል ውጪ ያሉ ጉዳዮችን ወደኋላ መረጃ እስከተገኘበት ጊዜ ድረስ በመሄድ ለጉዳዮች እልባት ለመስጠት ያግዛል፡*

***ስጋቶች***

- *በክስ እና በሌሎች የሽግግር ፍትህ አላባዎች መካከል ልዩነት ስለሚፈጥር የማዳላት ስሜት ሊሚፈጥር ይችላል፡*

- *በተወሰነ ቡድን ወይም የህብረተሰብ ክፍል ላይ ያነጣጠረ ነው የሚል ቅሬታ ያስነሳል፡*

- *ከህገ-መንግስቱ በፊትም ሆነ በኋላ መንግስት የሆነው ኢህአዴግ ሆኖ ሳለ የሽግግር መንግስት ወቅትን አለማካተት በተጎጂዎች ላይ የፍትህ መጓደል ስሜት በመፍጠር በሂደቱ ቅቡልነት ላይ ጥያቄ ያስነሳል።*

Draft

### 2.9.2. በሽግግር ፍትህ ሂደቱ የክልሎች/የከተማ መስተዳድሮች ሚና

የፌዴራል ስርአት ባላቸው ሀገራት - እንደ ሽግግር ፍትህ ያሉ ማዕከላዊ ተቆጣጣሪነትን፣ መሪነትን ወይም አስተባባሪነትን የሚጠይቁ አገርአቀፍ ሂደቶችን በሚመለከት ፖሊሲ የማውጣት እና የመተግበር ሀላፊነት ለፌዴራል መንግስቱ የሚሰጡ ስልጣኖች ናቸው።

በኢትዮጵያ የሚታሰበው የሽግግር ፍትህ ሂደት የሚተገበረው በአገር አቀፍ ደረጃ ነው። ስለሆነም በመላው አገሪቱ የሚካሄደውን ሁለንተናዊ የሽግግር ፍትሕ እንቅስቃሴና ተግባራት በተቀናጀ መልክ መፈጸም ማዕከላዊ መሪን የሚፈልግ በመሆኑ ሀላፊነቱን ለፌደራል መንግስት መሰጠቱ ተገቢ ይሆናል። ከዝርዝር ህጎች አንፃር ከታየም - ለምሳሌ በሽግግር ፍትህ ሂደት በወንጀል ክስ ውስጥ ይካተታሉ ተብለው የሚታሰቡት ከፍተኛ የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶች በአብዛኛው የፌዴራል መንግስቱ ስልጣን ስር የሚወድቁ ናቸው።

በተግባርም ከሌሎች አገራት ልምድ እንደታየው - በተለይ የብሄር ብዝሀነት እና ክፍፍል  ባለባቸው አውዶች - የሽግግር ፍትህ ሂደቶች የመጠለፍ እና ብሄርን መሰረት ላደረጉ ተጨማሪ ቁርሾዎች ምክንያት የመሆን አደጋ ሊያስከትሉ ይችላሉ። ይህንን ለመከላከል ዋንኛው መንገድ የሽግግር ፍትህ ሂደትን በማእከላዊ/በፌዴራል መንግስት እንዲመራ ማድረግ  ነው።

ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ - በሽግግር ፍትህ ሂደቱ የክልል እና የከተማ መስተዳደሮች ድርሻና አስተዋፅዖ ምን መሆን አለበት የሚለውን ጥያቄ በጥልቀት ማየት እና መወሰን ያስፈልጋል። በአንድ በኩል በሂደቱ የሚካተቱ ጥሰቶች እና የሚሳተፉ ግለሰቦች በእነዚህ ስፍራዎች ያሉ በመሆኑ፣ በሌላ በኩል አንዳንዶቹ ከፍተኛ ጥሰቶች በክልል ምህዳር ውስጥ የተፈፀሙ ሊሆኑ ስለሚችሉ - ክልሎች በሕግ ከተሰጣቸውን ስልጣን ብቻ ሳይሆን አጠቃላይ የፌዴራል ስርአቱ የሚተገበርበትን መንፈስ ከግምት ውስጥ በማስገባት የክልሎችን ሚና መወሰን ለሁለንታዊ አተገባበሩ እና ውጤታማነቱ ወሳኝነት አለው።

በኢትዮጵያ ለመተግበር በሚታሰበው የሽግግር ፍትህ ሂደት የክልሎች ተሳትፎ እና ሀላፊነት በፖሊሲው ሆነ ተከትለው በሚወጡ ህጎች ላይ በግልፅ ሊቀመጥ ይገባል። ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ - ክልሎች በሽግግር ፍትህ ሂደቱ ትርጉም ያለው የህዝብ ተሳትፎ እንዲኖር የማድረግ፣ ለሂደቱ ስኬት አስፈላጊውን እገዛና ድጋፍ የመስጠት፣ ክልላዊ አውድ ያላቸውን ጥሰቶች በሂደቱ እንዲካተቱ የማድረግ፣ ባህላዊ የፍትህ እና እርቅ ስርአቶች ለሽግግር ፍትህ ሂደቱ ሊሰጡ የሚችሉትን አስተዋጾ በማመላከት እንዲካተቱ የማድረግ፣ የአካባቢ አስተዳደሮችን የሲቪል ማህበራትን እና ሌሎች አቅሞችን በማስተባበር በእውነት እና እርቅ ሂደቶች ላይ ተሳትፎ እንዲኖራቸው የማድረግ ሀላፊነት አለባቸው።

በአጠቃላይ የሽግግር ፍትህ ሂደቱ ውጤታማ እንዲሆን - ክልሎች ከፌዴራል መንግስቱ ጋር በመናበብ እና በመቀናጀት ተግባራቶቻቸውን መፈጸም ይኖርባቸዋል። ይህንን ለማሳካት የሚያስችሉ ተገቢ አደረጃጀቶች ሊኖሩ የሚገባ ሲሆን - በአንዳንድ ሀገሮች ተመክሮ እንደታየው በክልል ደረጃ ከሚመለከታቸው አካላት የተውጣጣ የሽግግር ፍትህ ሂደቱ አማካሪ ኮሚቴ/ምክር ቤት ማቋቋምም ጠቃሚ ሊሆን ይችላል።

### 2.9.3. የባህላዊ ፍትህ ሥርአቶች ሚና

ሀገራዊ ወይም ባህላዊ የፍትሕ ሥርአት የሚባሉት አገር-በቀል የሆኑ፣ ከመደበኛው የፍትሕ ሥርአት የተለዩ፣ ባህልን፣ እምነትን፣ ትውፊትን መሰረት ያደረጉ - ፍርድ ወይም ፍትሕ ለመስጠት በማሕበረሰቡ የዳበሩ እና ማሕበረሰቡን የሚያገለግሉ መደበኛ ያልሆኑ የፍርድ እና ፍትሕ አማራጮች ናቸው። እውነትን ለማውጣጣት የሚደረጉ የባህልና የእምነት ሥርአቶችን፣ ፍርድ በመስጠት ሂደት ተቃራኒ ወገኖች ሙግት የሚያካሂዱባቸው ስርአቶችን፣ ባህላዊ እና የእምነት አስተምህሮ እና እሳቤዎችን መሰረት ያደረጉ ፍርዶችና የካሳ ውሳኔዎችን፣ ተቃራኒ ወገኖችን በባህልና በእምነት አስተምህሮና እሳቤ መሰረት የማስታረቅ ሂደቶችን፣ እና ከግጭት አፈታት ጋር የተያያዙ - አልፎም ግጭቶችን ለመከላከል የሚያስችሉ መሰል የባህልና የእምነት ክንውኖችን ያጠቃልላል።

በሽግግር ፍትህ ሂደት ባህላዊ የፍትህ ስርአቶች ከፍተኛ ሚና ሊጫወቱ ይችላሉ። በአንዳንድ ሂደቶች በተለይም እውነትን በማፈላለግ፣ በምህረት እና የእርቅ ሂደቶች ውስጥ መደበኛ የፍትህ ስርአቱን ከባህላዊ ስርአት ጋር በማቀናጀት የተሳኩ ተመክሮዎች አሉ። በእርግጥ አንዳንድ ባህላዊ ሂደቶች መብቶችን በማክበር፣ የሴቶችን ተሳትፎ በማረጋገጥ ረገድ፣ እንዲሁም ከፖለቲካ እና ሌሎች ተፅእኖዎች ነፃ ያለመሆን ችግሮች ይስተዋሉባቸዋል። እንደኢትዮጵያ አይነት የብሄር እና የሀይማኖት ብዝሀነት ባለባቸው ሀገራት - ሀገራዊ ቅቡልነት ያላቸው በሁሉም ቦታ ተግባራዊ ሊደረጉ የሚችሉ ባህላዊ ሂደቶችን ማግኘት አስቸጋሪ ሊሆን ይችላል። ስለሆነም ሂደቶቹን በማጥናት እና በመለየት በተገቢው መንገድ በሂደቱ ውስጥ እንዲተገበሩ ማድረግ ያስፈልጋል።

በኢትዮጵያ ለመተግበር የሚታሰበው የሽግግር ሂደት - ለአማራጭ ባህላዊ ስርአቶች እውቅና በመስጠት - የሚሸፍኗቸው ጉዳዮችን እና ስፍራዎችን በመለየት - አስተዋፅዖ ሊያበረክቱ በሚችሉበት ስፍራ ሁሉ ተግባር ላይ እንዲውሉ ማድረግ ይኖርበታል። ባህላዊ የእውነት ማፈላለጊያና እርቅ ማስፈኛ እሴቶች እና ስልቶች ለእውነት ማፈላልጉ፣ ይፋ ማውጣት  እና እርቅ ማስፈን ከቀረቡት ተቋማዊ አማራጮች ጋር - ሰብአዊ መብቶችን በሚያከብር መልኩ መጠቀም ይገባል። ይህም በሂደቱ ላይ የሚሳተፉ ተቋማትን ጫና በመቀነስ - በሽግግር ፍትህ ሂደቱ ዘላቂ ሰላም፣ ፍትህ እና እርቅ በማምጣት ስኬታማ እንዲሆን አስተዋፅኦ ያደርጋል።

## ክፍል 3

## የሽግግር ፍትህ ሂደቱ ሊመራባቸው የሚገቡ መርሆዎች እና የማስተባበር አደረጃጀት አማራጮች

### 3.1. የሽግግር ፍትህ ሂደቱ ሊመራባቸው የሚገቡ መርሆዎች

በሀገራችን የሚታሰበው የሽግግር ፍትህ ሂደት የሚከተሉትን መርሆዎች ባማከለ መልኩ የሚቀየስ እና የሚተገበር መሆን ይኖርበታል።

**ሀገራዊ ባለቤትነትን ማረጋገጥ፡**

የሽግግር ፍትሕ ሂደት - በመሰረቱ - አንዲት አገር በራሷ ለራሷ ተግባራዊ የምታደርገው ፍፃሜ ነው። ሂደቱ ሊመራ የሚገባው በራስ ተቋማት እና ዜጎች ነው። ይህም የአገር ሉአላዊነት መርሕን በመጠበቅ የብሔራዊ ኩራት መገለጫ ጭምር ሆኖ እንዲታይ ያደርገዋል፣ ቀጣይት ላለው የህግ የበላይነት እና ዘላቂ ተቋማዊ ግንባታም መሰረት የሚጥል ይሆናል።

**ዐውድ-ተኮር፣**

የሽግግር ፍትሕ አቀራረጽ እና አተገባበር ከማሕበረሰብ የፍትሕና እርቅ እሳቤዎችና ፍላጎቶች የፈለቀ፣ ዐውዳዊ ልዩ ሁኔታዎችን ያገናዘበ መሆን ይኖርበታል። በተጨማሪም በተጋለጠ ሁኔታ ውስጥ ያሉ ሴቶችና ሕጻናት እንዲሁም ሌሎች አካላት ያሉበትን ሁኔታ ጨምሮ የግጭቱን ባህሪና ያስከተለውን የመብቶች ጥሰት ይዘት ያገናዘበ መሆን ይኖርበታል።

**የህዝብ ተሳትፎን ማረጋገጥ፣**

የሽግግር ፍትህን ለመተግበር የሚደረግ የትኛውም ዓይነት ተቋማዊ አደረጃጀት የህዝብ ተሳትፎ እና ህጋዊነትን፣ የሂደቱን ነፃነት፣ ገለልተኝነት፣ ብቃት፣ አካታችነት፣ ውጤታማ እና ቀልጣፋ ክዋኔ፣ በቂ የሃብት ክፍፍልን፣ እና የስልጣን ግልፅነትን እና በቂነትን መሰረት ያደረገ መሆን አለበት።

**አካታችነት፣**

የሽግግር ፍትህ ሂደት በሁሉም ምዕራፎች ሁሉንም አካላት በእኩልነትና በፍትሀዊነት ሊያሳትፍ ይገባል። እንዲሁም እንደ ሴቶችና ልጃገረዶች፣ አረጋውያን፣ አካል ጉዳተኞች እና ወጣቶች ያሉ የተገፉ፣ የተገለሉና ተጋላጭ የሆኑ የሕብረተሰብ ክፍሎችን ልዩ ሁኔታና ፍላጎት መሰረት ያደረገ መሆን ይኖርበታል።



Draft

**የተቀናጀ አተገባበር፡**

*በተጨማሪም ሂደቱ የተለያዩ የሽግግር ፍትህ ስልቶች እና መንገዶችን በማቀናጀት በተናበበ መልኩ ለመተግበር እና ውጤት ለማስገኘት የሚያስችል ሊሆን ይገባል። አንዱን የሽግግር ፍትህ ዘዴ ብቻ ተግባር ላይ ማዋል ወይም የተለያዩ መንገዶችን ሳያቀናጁ በስራ ላይ ማዋል የተሳካ ውጤት እንዳይገኝ ያደርጋል። በተጨማሪም ቁጭቶችን እና ጥያቄዎችን በመፍጠር ከሚያስገኘው ጥቅም ይልቅ ጉዳቱ ያመዝናል። ስለሆነም የተሳካ የሽግግር ፍትህ ሂደት በሀገራችን እንዲኖረ ካስፈለገ አንዱ የሽግግር ጊዜ ፍትህ መንገድ ሌላውን የሚተካ ሳይሆን፡ ሁሉም የሚደጋገፉ እና የሚመጋገቡ መሳሪያዎች እንደሆኑ በመገንዘብ - በመደጋገፍ እና በትብብር እንዲተገበሩ ማድረግ ያስፈልጋል።*

**የሽግግር ፍትሕ አላባዎችን ቅደም ተከተል እና ሚዛን መጠበቅ፡**

*የሽግግር ፍትሕ አማራጭ ሥልቶችን በማጣመር ለመተግባር የሚደረግ ውሳኔ በአንድ ወገን የሰላምና እርቅ፡ በሌላ ወገን የኃላፊነትና ተጠያቂነት ግቦችን እርስ በእርስ ለማጠናከር እና ተመጋጋቢነታቸውን ለማስጠበቅ፡ እንዲሁም አካታች እድገትን ለማምጣት ያለመ መሆን ይኖርበታል።*

**ገለልተኛነት**:

*አሰራሩ በሽግግር ፍትህ ሂደትና አተገባበር ላይ ተሳታፊ በሆኑ አካላት መካከል መተማመንን መገንባት የሚያስችል፡ ወገንተኛ ያልሆነ፡ በአላማና በመርህ ላይ የተመሰረተ መሆን ይኖርበታል።*

### 3.2. የማስተባበር አደረጃጀት አማራጮች

*በኢትዮጵያ ለሚተገበረው የሽግግር ፍትህ ሂደት ከላይ ከተቀመጡት የትኛውንም አማራጭ ብንከተል - ተግባራቶቹ ከአንድ በላይ በሆኑ ተቋማት መከናወናቸው አይቀርም። አዲስ ኮሚሽን በማቋቋም የሽግግር ሂደቱን ማከናወን የሚለው አማራጭ በክፍል ሁለት በተደጋጋሚ ቀርቧል። ኮሚሽኑ አንዳንዶቹን ስልቶች በባለቤትነት የሚመራ፡ ሌሎች ተቋማትንም የሚያስተባብር እና የሚያቀናጅ ይሆናል። ስያሜው የሀቅ እና የእርቅ ኮሚሽን፡ ወይም የእርቅ እና የሰላም ኮሚሽን፡ ወይም የእውነት እና እርቅ አፈላላጊ ኮሚሽን፡ ወይም የሀቅ፡ የፍትህ እና የእርቅ ኮሚሽን ሊባል ይችላል። ይህም ተቋቁሞ ከነበረው የእርቀሰላም ኮሚሽን ትምህርት በመውሰድ፡ እና አለማቀፍ ልምዶችን ግምት ውስጥ በማስገባት - በህግ የሚሰጡትን ስልጣን እና ሀላፊነቶች መወጣት የሚችል ተቋም ማደራጀትን ይጠይቃል።*

*ይሁንና ይህ አዲስ ኮሚሽን የማቋቋም አማራጭ ተቀባይነት ቢያገኝ እንኳ - ቢያንስ ክስ ከመመስረት እና ከማካካሻ ስርአት አንፃር የመሪነት ሚና የሚጫወቱ ሌሎች ተቋማት ሀላፊነት ይኖርባቸዋል። በመሆኑም እነዚህን ተግባራት የማቀናጀት እና የማስተባበር ተግባር የሚቀር አይደለም። ስለሆነም ስኬታማ እና የተሟላ ሂደት እንዲኖር ለማድረግ በሂደቱ ሀላፊነት ያለባቸውን ተቋማት ለማስተባበር የሚስፈልገውን አደረጃጀት መተለም ያስፈልጋል። ስለሆነም ፖሊሲውን በባለቤትነት የሚያስፈፅም እና በአተገባባሩ ላይ ክትትል የሚያደርግ ብሄራዊ የሽግግር ፍትህ አስተባባሪ ቦርድ (ምክር ቤት) ማቋቋም አስፈላጊ ይሆናል።*

*ከዚህ በተጨማሪ በተጠቀሰው የማስተባበር አደረጃጀት ላይ አዲስ አቅም በማቀም - ከላይ ከተቀመጡት ሁለት ተቋማዊ አማራጮች ጠንካራ ጎኖች እና ስጋቶችን በማቀናጀት የተለየ አደረጃጀት የሚፈጠርበት እድል ሊኖር ይችላል። ይህ አማራጭ የሚከተለው መልክ ይኖረዋል።*

**ብሄራዊ የሽግግር ፍትህ አስተባባሪ ቦርድ (ምክር ቤት) ማቋቋም፡**

*ተቋሙ የሽግግር ፍትህ ፖሊሲውን በባለቤትነት የማስፈፀም እና በፖሊሲው መሰረት ተቋማት ተግባሮቻቸውን ማከናወናቸውን የማረጋገጥ ሀላፊነት ይኖርበታል። እንደ አግባብነቱ ተመሳሳይ አደረጃጀቶች በክልል ደረጃም ሊቋቋሙ ይችላሉ።*

Draft

አባላቱም በፖሊሲው ላይ የተጠቀሱ ተግባራትን ለመፈፀም፡ ለመቆጣጠር ወይም ለመደገፍ ሀላፊነት ካለባቸው ተቋማት የተወከሉ፡ እንዲሁም በነፃና አሳታፊ ሂደት ከባህላዊ አደረጃጀቶች እና ከህብረተሰቡ የሚመረጡ ሰዎች ይሆናሉ። ዝርዝር ጉዳዩ በህግ የሚወሰን ቢሆንም የሚፈጠሩ አዲስ ተቋማትን ጨምሮ በውክልና የሚመደቡት የቦርዱ አባላት ከሚከተሉት ተቋማት የሚወከሉ ሊሆኑ ይችላሉ - ከህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት፡ ከፌዴራል ፍርድ ቤቶች፡ ከፍትህ ሚኒስቴር፡ ከፌዴራል ፖሊስ፡ ከኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን፡ ከብሄራዊ ምክክር ኮሚሽን፡ ከባህላዊ ስርአቶች፡ ከታዋቂ ሰዎች፡ እና ከሀገር ሽማግሌዎች።

ከህብረተሰቡ የሚመረጡ አባላትን በሚመለከት - አዲስ ኮሚሽን ቢቋቋም አባላትን በመመልመል ሂደት ሊኖር የሚችለው ነፃ እና ገልልተኛ አካሄድን በመከተል የሚሰየሙ መሆን ይኖርባቸዋል።

የኮሚሽኑ ሰብሳቢ እና የሚቋቋመው ሴክሬታሪያት ሀላፊነት በነዚህ አባላት የሚያዝ ይሆናል። የቦርዱ አባላት በሙሉ ተአማኒነት እና መልካም ስብእና ያላቸው፡ በህብረተሰቡ ዘንድም የሽግግር ፍትሁ ባለቤቶች ተደርገው ሊሳሉ የሚችሉ መሆን ይኖርባቸዋል።

**ብሄራዊ የሽግግር ፍትህ አስተባባሪ ቦርድ ሴክሬታርያት፡**

አስተባባሪ ቦርዱ በሽግግር ፍትህ ሂደቱ በተቋማቱ በቀጥታ የማይከናወኑ ተግባራትን የሚያከናውንበት፡ እንዲሁም የማስተባበር ሀላፊነቱን የሚወጣበት በባለሙያዎች የተመላ ሴክሬታሪያት ይኖረዋል። አዲስ ኮሚሽን ከተቋቋመ ሴክሬታርያቱ በኮሚሽኑ ስር የሚደራጅ ይሆናል። ይህ ካልሆነ ግን በሌሎች ሀገሮች ልምድ ለኮሚሽኖች የሚሰጡ እንደ እውነትን ማጣራት፡ ምህረት፡ የእርቅ ሂደቶች እና የማካካሻ ሂደት ጉዳዮች ላይ ሴክሬታርያቱ መመሪያዎችን ያዘጋጃል፡ እንደ አግባብነቱ ይፈፅማል፡ ተግባራቱ በሌሎች ተቋማትም ትኩረት ተሰጥቷቸው እንዲፈፀሙ የማድረጊያ አቅም ይሆናል።

## 4. ማጠቃለያ

በሽግግር ውስጥ ያለ ማህበረሰብ ከነበረበት የጦርነት፡ የእርስ በእርስ ግጭት እና አምባገነናዊ ጭቆና ለመውጣት የሽግግር ፍትህን ተግባራዊ እንደሚያደርግ ተመልክቷል። የሽግግር ፍትህ ሀሳቡ፡ አተገባበሩ እና ስልቶቹ ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደጉ የመጡ በመሆኑ - በአሁኑ ሰአት የሚተገበር የሽግግር ፍትህ ፖሊሲ ከቀደምት የሽግግር ፍትህ አተገባበሮች እና ስልቶች ብዙ ልምድ በመውሰድ ውጤታማ እየሆነ መጥቷል።

ኢትዮጵያ በሽግግር ሂደት ውስጥ እያለፈች የምትገኝ አገር እንደመሆኗ መጠን የሽግግር ፍትህን የግድ ተግባራዊ ማድረግ የሚገባት መሆኑን የሚያመላክቱ በርካታ ጉዳዮች አሉ። በተለይም ሀገራዊ አውዱ የተሟላ የሽግግር ፍትህ ስርዓት ሂደትን መተግበር አስፈላጊ እንደሆነ የሚያሳይ ነው። የተሳካ የሽግግር ፍትህ ሂደት ለሀገረ መንግስቱ ግንባታ እና ቀጣይነት ገንቢ ሚና ይጫወታል። የተሳካ የሽግግር ፍትህ ሂደት ሳይተገበር የዲሞክራሲ ሽግግርም ሆነ ዘላቂ ሰላም ማረጋገጥ አይቻልም። በተጨማሪም - የሽግግር ፍትህ ሥርዓትን መተግበር ለሰብአዊ መብቶች መከበር እና ለህግ የበላይነት መረጋገጥ መሰረት የሚጥል መሆኑ እንደምክንያት ማንሳት ይቻላል።

ከዚህ በፊት የተተገበሩት የሽግግር ፍትህ ስልቶች በእርቅና ሀገራዊ መግባባት ላይ ያተኮሩ ባለመሆናቸው ውጤታማ አልነበሩም። ከነዚህ የቀደሙ ተመክሮዎች በመማር ውጤታማ የሆነ የሽግግር ፍትህ ስርዓት ትግበራ አቅጣጫ በፖሊሲ ማስቀመጥ እና ተግባራዊ ማድረግ እጅግ አስፈላጊ ይሆናል። ለዚህም አለማቀፍ ልምድን በመቀመር እና የሽግግር ፖሊሲ አማራጮችን ከሀገራችን ነባራዊ ሁኔታ አንፃር በማዘጋጀት - ህብረተሰቡ እና ባለድርሻ አካላትም ተወያይተውበት እንዲፀድቅ በማድረግ - አስፈላጊውን የህግ ማእቀፍ በማዘጋጀት ወደ ተግባር መግባት ያስፈልጋል።

Draft